# መከተል

## በክርስቶስ ያገኛችሁትን ሕይወት ማወቅ



# መከተል

## በክርስቶስ ያገኛችሁትን ሕይወት ማወቅ






# ፖል ጎትሃርድት

ትርጉም፥ ተመስገን ሳህለ

አርትዖት፥ ዘላለም መንግሥቱ

በተለየ ሁኔታ ካተገለጸ በስተቀር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ሁሉ የተጠቀሱት
በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ከታተመው የ1954 ዕትም መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

Copyright © 2012 by *Life Baptist Church* in Las Vegas

# ሕይወት ስለ ግንኙነት ነው።

## ስለ መጽሐፉ፤

መከተል የክርስቶስ ኢየሱስ ሕይወት ሦስት ቁልፍ ግንኙነቶች የእናንተን ደቀ መዝሙራዊ ዕድገት እንዴት ተጽእኖ እንደሚያሳርፉበት ያመለክታል። ኢየሱስ ከአብ ጋር፥ ከቤተ ክርስቲያን ጋር እና ከዓለም ጋር በትክክለኛ ግንኙነት ነበር የኖረው። ሦስቱም ግንኙነቶች ተገቢ በሆነ ውጥረት ውስጥ ነበር የቆዩት። በቀጣዮቹ አራት ሳምንታት በሦስቱ ግንኙነቶች በእያንዳንዳቸው ውስጥ ክርስትና እንዴት እንደሚሠራ ትመለከታላችሁ።

ክርስቶስን መከተልን ስትማሩ ለእግዚአብሔር የጠለቀ ፍቅርን እያጎለበታችሁ ትሄዳላችሁ። እግዚአብሔርን በመውደድ ከአብ ጋር ያላችሁን ግንኙነት ታተኩራላችሁ። ክርስቶስን ስትከተሉ እርሱ ከአማኞች ጋር አንድ የመሆን ጠቀሜታ ላይ ያተኩራል። ክርስቶስ የእርሱን ደቀ መዛሙርት ከቤተ ክርስቲያን ጋር በትክክለኛ ግንኙነት እንዲሆኑ የመራባቸውን አቅጣጫዎች ትመለከታላችሁ። በመጨረሻም ክርስቶስን መከተል ዓለምን (ሰዎችን) እንድታገለግሉ እና ወንጌልን በአደራ እንድታስተላልፉ ይሞግታችኋል። ሁለቱም ተግባራት በዓለም ውስጥ እግዚአብሔርን በሚያከብሩ አቅጣጫዎች እንድትሳተፉ ያበረታቷችኋል። በጊዜ ሂደት ዓለምን በግንኙነት መነጽር ትመለከታላችሁ።

መከተል በሳምንት ስድስት የጽሞና ክፍሎችን በያዙ አራት ሳምንታት የተከፋፈለ ነው። ለአንድ ወይም ሁለት ቀን ወደ ኋላ ከቀራችሁ ችግር የለውም። ነጻዎቹ ቀናት አሚልታችሁ ለመሄድ እንድትችሉ ጊዜ ይሰጧችኋል። መምሪያውን ለማጠናቀቅ ከሠላሳ ቀናት በላይ የምትፈልጉ ከሆነ፥ ያም መልካም ነው። ይሄ ለማገዝ የተዘጋጀ መምሪያ ነው እንጂ እንድትታዘዙት የሚያስገድድ ሕግ አይደለም! ከእግዚአብሔር ጋር ሆናችሁ በምታሳልፉት ጊዜ ተደሰቱ። በእርሱ ላይ አተኩሩ። ማስታወሻዎችን ያዙ፤ ብሎም የግል የጽሞና ጊዜያችሁን እርሱ ወደ ግንኙነት ዕድገት ሲለውጠውም አስተውሉ።

እርሱን እየተከተላችሁ በምትሄዱበት ጊዜ እግዚአብሔር ይባርካችሁ!

መከተል


**1ኛ ሳምንት፡ እግዚአብሔን ውደዱ - - - - - - - - - - - - - - - - - - - - 6**

1ኛ ቀን፡ አንድ ነገር ብቻ ማድረግ ቢቻላችሁ . . .

2ኛ ቀን፡ ፍቅርን ቀላል እንደሆነ መጠበቅ

3ኛ ቀን፡ እርሱ እየጠበቃችሁ ነው

4ኛ ቀን፡ እግዚአብሔር የሚወደድ ነውን?

5ኛ ቀን፡ የእውነት ከወደዳችሁኝ . . .

6ኛ ቀን፡ ለምን እግዚአብሔርን በቤቱ ብቻ ማምለክ አልችልም?

**2ኛ ሳምንት፡ ከአማኞች ጋር አንድ መሆን - - - - - - - - - - - - - - - - - 20**

1ኛ ቀን፡ የመበረታቻ ስፍራ

2ኛ ቀን፡ ሰዋዊ ገጽታ

3ኛ ቀን፡ ለስግብግብነት ሕይወት የቀረበ ተግዳሮት

4ኛ ቀን፡ ከክብደት ማንሻ ክፍል የሚገኙ ትምህርቶች

5ኛ ቀን፡ የማኅበረሰብ/ኅብረት የሕይወት ዘይቤ የምርጫ ጉዳይ ነው

6ኛ ቀን፡ አንዳችን ሌላችንን ማገልገል

**3ኛ ሳምንት፡ ዓለምን አገልግሉ - - - - - - - - - - - - - - - - - - - - 34**

1ኛ ቀን፡ ምልካሙን ሥራችሁን እንዲያዩ

2ኛ ቀን፡ ዕቅድ አንድ ላይ ሲመጣ

3ኛ ቀን፡ የምንከተላቸውን መምሰል

4ኛ ቀን፡ በትዕቢት ላይ እርምጃ መውሰድ

5ኛ ቀን፡ እንደዚህ ጊዜ ሙሉነት (እርካታ) ተሰምቶኝ አያውቅም

6ኛ ቀን፡ ክርስቶስን ለማካፈል ምቹ ዐውድ መፍጠር

**4ኛ ሳምንት፡ ወንጌሉን አደራ ስጡ - - - - - - - - - - - - - - - - - - - - 48**

1ኛ ቀን፡ አደራ መሰጠት (በማንኛውም ነገር) ማለት ምን ማለት ነው?

2ኛ ቀን፡ ወንጌሉን አደራ መስጠት

3ኛ ቀን፡ የግንኙነት ጎዳናዎች

4ኛ ቀን፡ የወንጌሉን አደራ ማስተላለፊያ ቀላሉ መንገድ

5ኛ ቀን፡ የወንጌሉ የላቀ መስፋት ወይም ታላቅ ዕድገት

6ኛ ቀን፡ በ ‘ከ . . . እስከ . . .’ መስመር ምን ታደርጋችሁ?




ሳምንት አንድ
እግዚአብሔርን ውደድ።

## 1ኛ ቀን፥ አንድ ነገር ብቻ ማድረግ ቢቻላችሁ . . .

የዕረፍት ጉዞው ሁለት ሳምንት ብቻ ስለቀረው አራጋው የመጨረሻ ዕቅዱን እያወጣ ነበር። በሂደቱ ውስጥ የስድስት ዓመት ልጁን ለማሳተፍ በመፈለግ አራጋው እንዲህ ብሎ ጠየቀው፤ “ባሕር ዳርቻውጋ ስንደርስ ልታደርገው የምትፈልገው ነገር አለን?” በጥቂት ሰኮንዶች ውስጥ ልጁ አስደናቂ ሊባሉ የሚችሉ በርካታ ነገሮችን ዘረዘረ። የዝርዝሩን ብቻትና ያለውን የገንዘብ መጠን በማሰብ አራጋው ጥያቄውን እንዲህ ብሎ አስተካከለው፤ “በባህር ዳርቻው ልታደርገው የምትችለው አንድ ነገር ብቻ ቢሆን የምታደርገው ነገር ምንድን ነው?” ለማሰብ በርካታ ደቂቃዎችን ከወሰደ በኋላ ልጁ ሳቅ አለና እንዲህ አለው፤ “በእውነቱ ምንም ነገር ብናደርግ አብረን እስካደረግነው ድረስ ችግር የለውም።”

የክርስቲያን ጉዞ ይህንን ታሪክ ሊመስል ይገባል። ገና በመጀመሪያ ምልከታ እንደ ክርስቲያን ሊታሰቡ እና ሊደረጉ የሚገባቸው በጣም በርካታ ነገሮች አሉ። ልንጸልይ፣ ቃሉን ልናጠና፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን ልንሄድ ለመልካም ሥራ ልንለግስ፣ ሌሎችን ልናገለግል፣ እምነታችንን ልናካፍል እና ሌሎችም ብዙ ነገሮችን ልናደርግ እንችላለን። ክርስትና መልካም ተግባራት የሚያጥሩት አይደለም። ነገር ግን በክርስትና ልብ ውስጥ ያለው ነገር ከክርስቶስ ጋር የመሆን ጥሪ ነው።

ኢየሱስ የመጀመሪዎቹን ደቀ መዛሙርት በጠራ ጊዜ ማርቆስ እንደመዘገበው “<u>ከእርሱም ጋር እንዲኖሩና</u> ለመስበክ እንዲልካቸው፥ . . . አሥራ ሁለት አደረገ።” (ማር. 3፥14-15)። ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ ነበር የተጠሩት፤ አናም ከዚያ እርሱ ለአገልግሎት ወደ ውጪ ይልካቸው ዘንድ። እዚህጋ አትኩሮቱ በግንኙነት ላይ ነው። <u>በክርስትና ሕይወት ልታደርጉ የምትችሉት አንድ ነገር ብቻ ከሆነ ጊዜን ከክርስቶስ ጋር አሳልፉ።</u>

እግዚአብሔርን በመውደድ ላይ ስታተኩሩ ወደ የት እንደምትሄዱ ምን እንደምታደርጉ እና እንዴት እንደምታደርጉት የመሳሰሉት ጉዳዮች፥ ከማን ጋር ከመሆናችሁ ጋር ሲነጻጸር ሁል ጊዜ ሁለተኛ ስፍራ የሚሰጣቸው እንደሆኑ አስታውሱ።

በየዕለቱ ከኢየሱስ ጋር ልትሆኑ የምትችሉባቸውን ልዩ ልዩ መንገዶች ዘርዝሩ፤

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

በየዕለቱ ከክርስቶስ ጋር ለመሆን በመንገድ ላይ የሚጋረጡ እንቅፋቶች ምን ምን ናቸው?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**የጸሎት ጥቆማ፡** “ጌታ ኢየሱስ ላውቅህ እሻለሁ። በሕይወቴ የመጀመሪያ ቅድሚያ የሚሰጠው ነገር ከአንተ ጋር መሆን እንደሆነ ተረድቻለሁ። ይህንን መሻት ለማሟላት የሚያስችሉትን ልዩ ልዩ አቅጣጫዎች እና በአቅጣጫዬ ላይ የሚቆሙ ልዩ ልዩ እንቅፋቶችን አሳይተኸኛል። በየዕለቱ ከአንተ ጋር ለመሆን መለወጥ የሚገባቸው ነገሮችን ለመለወጥ እንድችል ድፍረትን ስጠኝ። በኢየሱስ ስም እጸልያለሁ። አሜን!”

**ለተጨማሪ ጥናት የሚሆኑ ምንባባት፡** ዮሐንስ 15፡1-5፤ 17፡3፤ ሉቃስ 10፡38-42፤ ዘዳግም 6፡4-5፤ መዝሙር 1፤ 27፡4-6።

ማስታወሻ፤

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

## 2ኛ ቀን፥ ፍቅርን ቀላል (ያልተወሳሰበ) እንደሆነ መጠበቅ

በቅርቡ ለፍቅረኛው የጋብቻ ጥያቄውን በትልቅ ባነር ላይ፥ "እባክሽ አግቢኝ" የሚል ጽሑፍ አሳትሞ በደጃፏ ላይ ያስተከለ ሰው ታሪክን ሰምቼ ነበር። እንዳለመታደል ሆኖ ማተሚያ ቤቱ በስሕተት 'ኝ' የሚለውን ፊደል 'ን' ብሎ ነበር ያተመው። ሰውየው ተስፋ እንዳደረገው አስደናቂ በሆነ መልኩ የቀረበ መሆን ባይችልም ልጅቱ መልእክቱ ገብቷት ነበር።

ለእግዚአብሔር ያላችሁን ፍቅር በአንድ የገዘፈ መንገድ ማረጋገጥ አስፈላጊ ስለመሆኑ ተሰምቷችሁ ያውቃልን? እግዚአብሔርን መውደድ በምናደርጋቸው ትላልቅ ነገሮች ወይም በምንሰጣቸው ስጦታዎች መጠን የሚለካ ነገር አይደለም። እግዚአብሔርን መውደድ ከእርሱ ጋር መሆን እና የእርሱን ጊዜ አክብሮ ስለመታዘዝ ነው።

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ፥ "የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን።" (ዮሐ. 14፥23) ብሏል።

በኢየሱስ አገላለጽ መሠረት ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር ከግንኙነት በሚፈልቅ ቀላል ወይም ባልተበረዘ መታዘዝ የሚገለጥ ነው። የበርካታ ክርስቲያኖች የመጀመሪያ ምላሽ "እንደምወደው ለማሳየት እግዚአብሔርን እታዘዛለሁ።" ማለት ነው። ይህ አባባል ተግባር-መራሽ በሆነ ሃይማኖት እና በራስ ላይ መደገፍን መሠረት ያደረገ ነው። ኢየሱስ ትምህርት እንድንወድደው እና ከዚያ መታዘዝ እንዲከተል ነው።

ኢየሱስን ለመውደድ አንታዘዘውም፤ ስለምንወድደው ግን እንታዘዘዋለን፤ የመውደዳችን ውጤቱ መታዘዝ ነው።

ዮሐ. 4፥19 ን አንብቡ። ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር መነሻው ምንድን ነው?

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

1ዮሐ. 4፥19 እኛ ፍቅርን እያነሳሳን ሳይሆን እርሱ ለእኛ ላለው ፍቅር ብቻ ምላሽ እየሰጠን መሆናችንን እንድንረዳ ይነግረናል። እግዚአብሔር ይወዳችኋል!

እግዚአብሔር የላቀ ደረጃ ላለው ቅርበት እያንዳንዳችንን እየጋበዘን እያለ እርሱ በልዩ መንገድ እንድንከተለው ፈጥሮናል። ከጌታ ጋር በጸጥታ ተቀመጡ እና “ዛሬ አንተን እንዴት ባለ መንገድ እንድከተልህ ትፈልጋለህ?” ብላችሁ ጠይቁት። እግዚአብሔር የተናገረውን መዝግቡ እና ተግብሩት!

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**የጸሎት ጥቆማ፤** “ጌታ ኢየሱስ፤ ላውቅህ እፈልጋለሁ። አንተን በመውደድ አቅጣጫዬ ላይ የሚገቡትን የኔን አንዳንድ ነገሮች በምሕረትህ ልታነሳልኝ ትወዳለህን? በሂደቱ ውስጥ ጸጋህ እንዲያግዘኝ እና የሚፈለገውን ለመልቀቅ ድፍረት እንዲኖረኝ እጸልያለሁ። ይህን በስምህ ጸለይኩ። አሜን!”

**ለተጨማሪ ጥናት የሚሆኑ ምንባባት፤** ሉቃስ 10፥38-42፣ ማርቆስ 12፥41-44፣ 1ኛ ዮሐንስ 2፥3-6

ማስታወሻ፤

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

## 3ኛ ቀን፥ "እርሱ እየጠበቃችሁ ነው"

*"ማለዳም ተነሥቶ ገና ሌሊት ሳለ ወጣ ወደ ምድረ በዳም ሄዶ በዚያ ጸለየ።"* ማርቆስ ፲፥35

ኢየሱስ በአንድ የገጠር ቤት ክፍል ውስጥ ጠረጴዛ ላይ ተቀምጦ የሚያሳይ ብዙም እውቅና የሌለው አንድ የቅብ ስዕል አለ። ጠረጴዛው ሁለት ወንበሮች ሲኖሩት ኢየሱስ አንደኛው ላይ ተቀምጧል። በጠረጴዛው ላይ የዘይት መቅረዝ፣ የተከፈት መጽሐፍ ቅዱስ እና ማስታወሻ ደብተር አለ። ከበስተጀርባ ባለው የተከፈተ ትንሽ መስኮት በኩል ፀሐይ በኮረብታው አናት በኩል ስትወጣ ይታያል። ስዕሉ የመረጋጋት እና ሰላማዊ ስሜት ያሳያል። ከዚያም ከስሩ ያለውን "እርሱ እየጠበቃችሁ ነው።" የሚሉትን ቃላት ታነባላችሁ።

እኔ ይህን ስዕል ለመጀመሪያ ጊዜ ስመለከት ከእግዚአብሔር ጋር ስለማሳልፈው ጊዜ ጥልቅ የሆነ ተጽእኖ አሳድሮብኛል። ላስብ የቻልኩት ነገር በአጠቃላይ ኢየሱስን በጠረጴዛው ላይ ለብቻው ትቼው የሄድኩባቸውን በርካታ ጊዜያት ነው። ምክንያቶቼ ማለቂያ የሌላቸው ነበሩ። በጣም ሥራ ይበዛብኝ፣ በጣም እደክም፣ እና በጣም በልዩ ልዩ የሕይወት ጉዳዮች እያዝ ነበር! ነገር ግን ምንም ያህል ማመካኛ ልስጥ፤ የቅብ ስዕሉ እያንዳንዳቸውን ጸጥ አሰኛቸው። ከዚህ ክርስቶስ በትዕግሥት እና በጸጥታ እኔ ከእርሱ ጋር ጊዜ እንዳሳልፍ እኔን እየጠበቀ ከሚያሳይ ምስል ጋር ብቻ ቀርቼ ነበር።

ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ ማሳለፍ የማይቻልና የሚያስፈራ ሊመስል ይችላል። ምን ታደርጋላችሁ? የት ትጀምራላችሁ? ምን ትላላችሁ? አንድ ቀን ቢያመልጣችሁ ምን ይሆናል? ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ ለማሳለፍ ቁልፉ በግንኙነቱ ላይ ማተኮር ነው። እዚያ ያላችሁት እርሱን ለማወቅ ነው። ባለፈው ሳምንት የተማርነውን አስታውሱ፤ የሕይወት የመጨረሻ ግብ እግዚአብሔርን ማወቅ ነው፤ የሕይወት የየዕለቱ ግብ ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ ማሳለፍ ነው።

በማርቆስ 1፥35 ላይ ባለው የኢየሱስ ልማድ መሠረት ጥብቅ ቅርርብን የመጀመሪያ ነገር ሲደርገው ልንመለከት እንችላለን። የእኛ ፈተና ወይም ሙግት የእርሱን የእግሩን ዱካዎች መከተል ነው።

- ማርቆስ ፲፡35 ከእግዚአብሔር ጋር የምታሳልፉትን ጊዜ በበለጠ ጽናት እና ቋሚነት እንድታሳድጉ እንዴት ይሞግታችኋል?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ምንባቡ ኢየሱስ ከአባቱ ጋር በተለየ ጊዜ፣ በተለየ ቦታ እና ለተለየ ምክንያት ይገናኝ እንደነበር ያስተምረናል። ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት የተለየ ዕቅድ ወይም ልማድ አላችሁን? ካልሆነ ለሕይወታችሁ የተለየ ዕቅድ ለማውጣት ለመዘጋጀት ጥቂት ጊዜ ውሰዱ።

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**የጸሎት ጥቆማ፤** "ጌታ ኢየሱስ ላውቅህ እሻለሁ። አንተን የማወቂያው ብቸኛው መንገድ ከአንተ ጋር ጊዜ ማሳለፍ እንደሆነ ተረድቻለሁ። አብረን በምናሳልፈው ጊዜ ትኩረቴ በግንኙነታችን ላይ እንዲሆን አድርጌ እንድይዝ እጸልያለሁ። በኢየሱስ ስም ጸለይኩ። አሜን!"

**ለተጨማሪ ጥናት የሚሆኑ ምንባባት፤** ሰቆቃው ኤርምያስ 3፥21-25፤ መዝሙር 33፥18-22፣ 46፥1-11፤ 1ዜና መዋልዕ 16፥9፤ ዕብራውያን 10፥19-22፤ ራእይ 3፥20።

ማስታወሻ፤

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

# 4ኛ ቀን፥ እግዚአብሔር የሚወደድ ነውን?

ከአንድ ሰው ጋር በፍቅር መውደቅ ምን ይፈልጋል? እያንዳንዱ ሰው ለዚህ ጥያቄ በጥቂቱ የሚለያዩ መልሶች የሚሰጥበት ዕድል አለ። ምናልባት የተሻለው ጥያቄ፥ "አንዳንድ መልካም ባህርያት ከሌሎች ባህርያት የበለጠ የሚወደዱ ናቸውን?" የሚለው ነው። ይሄ ትክክለኛው ሃሳብ ነው! አንድ ሰው አቶ መልካሙን ወይም ወ/ሮ መልካሟን እንደ ዕቡይ፣ ተስፋ አስቆራጭ፥ ውስጥና ውጪው የማይገናኙ፥ እና በጥቅሉ ጸለምተኛ አድርጎ ይገልጻል ማለት ያጠራጥረኛል። በቀኑ መጨረሻ ለምናደንቃቸው እና ለምንሻቸው መልካም ጎኖች መሳባችን አይቀሬ ነው።

ይህን ካልን በኋላ እግዚአብሔርን ተወዳጅ የሚያደርገው ምንድን ነው? የሕይወት ዓላማ ከክርስቶስ ጋር የፍቅር ግንኙነት እንዲኖር መፈለግ ከሆነ፤ ያ እግዚአብሔር የሚወደድ ስለመሆኑ ቅድሚያ ግምትን ይፈጥራል። ስለዚህ እግዚአብሔርን ተወዳጅ የሚያደርጉት ምልካም ባህርያት ምን ምን ናቸው?

የእግዚአብሔርን ባህርይ በፈጣን ለመግለጽ መዝሙር 103ን ለማንበብ ጥቂት ጊዜ ውሰዱ። በሃያ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ ስለ እግዚአብሔር የሚከተሉትን እናገኛለን፡-

| | | |
|---|---|---|
| ይቅር ባይ (ቁ. 3፣9፣12) | ነፍስን የሚያረካ (ቁ. 5) | ምሕረት የተሞላ (ቁ. 10) |
| አዳኝ (ቁ. 3) | ጻድቅ (ቁ. 6፣17) | ልበ ሰፊ (ቁ. 14) |
| ታዳጊ (ቁ. 4) | ገላጭ/አመልካች (ቁ. 7) | ዘላለማዊ (ቁ. 17) |
| አፍቃሪ (ቁ. 4፣8፣11፣17) | ለጋስ (ቁ. 8) | ሉዓላዊ (ቁ. 19) |
| ርኅሩኅ (ቁ. 4፣8፣13) | ለቁጣ የዘገየ (ቁ. 8) | ምስጋና የተገባው (ቁ. 20-22) |

ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር ስለ እግዚአብሔር ካለን እውቀት መቼም የበለጠ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ ስለ እግዚአብሔር ያለን እውቀት በጥልቀት በእርሱ የተገለጠ ባህርይ ላይ የተተከለ ሆኖ እንዲጸና ዋጋ ልንከፍል ይገባናል።

ጥቂት ጊዜ ወስዳችሁ የሚደነቁና የሚፈለጉ ሆነው ያገኛችኋቸውን ሌሎች የእግዚአብሔር መልካም ባህርያት ዘርዝሩ።

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**የጥሞና ጥቆማዎች፤** በየዕለቱ ቃን ስታነቡ እግዚአብሔር በቃሉ አማካኝነት ባህርይውን እንዲገልጥላችሁ ጠይቁት። የእግዚአብሔርን ባህርይ የበለጠ ስናውቅ እርሱን መውደድ የበለጠ በእውነታ ላይ የተመሠረተ ይሆናል።

**የጸሎት ጥቆማ፤** “ጌታ ኢየሱስ፤ ላውቅህ እሻለሁ። በበለጠ መንገድ ላውቅህ እችል ዘንድ ዛሬ ያንተ ባህርይ በእኔ ሕይወት ተገልጦ እንዳይ ትረዳኛለህን? ይህን በስምህ ጸለይኩ፤ አሜን!”

**ለተጨማሪ ጥናት የሚረዱ ምንባባት፤** ዘጸአት 15፥1-18፣ ዘዳግም 7፥7-9፣ መዝር 113፥145።

ማስታወሻ፤

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

## 5ኛ ቀን፥ የእውነት ከወደዳችሁኝ . . .

“የእውነት የምትወዱኝ ቢሆን _____ ታደርጉልኝ ነበር” በሚል ንግግር ወቀሳ ቀርቦባችሁ ያውቃልን? ምናልባት አንዳንድ ምሳሌዎች ትዝታችሁን ያነቃቁ ይሆናል። “የምር ብትወጂኝ ኖሮ ሽሚዜን ትተኩሺልኝ ነበር። የምር ብትወደኝ ኖሮ ይህንን ሰዓት ትገዛልኝ ነበር። የምር ብትወዱኝ ኖሮ እኔ ማድረግ የምፈልገውን ታደርጉ ነበር።” አለመታደል ሆኖ ፍቅር ሰዎችን የመቆጣጠሪያ መቆመሪያ መሣሪያ ሊደረግ ይችላል።

ይሄንን በአሳባችን ይዘን በዮሐንስ 14፥15 ላይ ያለውን የኢየሱስ ንግግር እንዴት ልንተረጉመው ነው? ኢየሱስ “ብትወዱኝ ትእዛዛቴን ትጠብቃላችሁ።” ብሏል። ይሄም ልክ “የምር የምትወዱኝ ቢሆን የተናገርኩትን ታደርጉ ነበር።” እንደማለት ነው?

ሆኖም በክርስቶስ ባህርይ መሠረት ፈጽሞ እኛን እንደማያስገድደን እናውቃለን። ታዲያ ይህንን ምንባብ ለመረዳት ስንሞክር የትጋ ነው የሚያደርሰን? ከክርስቶስ ጋር ስላለን ግንኙነት መንፈሳዊ ማጣሪያ መፈተኛ ይሆንልናል። ከእግዚአብሔር ጋር በምናደርገው ጉዞ ላይ ችግሮች የሚያጋጥሙን ከሆነ (ለምሳሌ ፍላጎት ማጣት፣ የተጓተተ ዕድገት፣ ኃጢአት ነክ ድግግሞሽ፣ ወዘተ...) ያ የፍቅር ጉዳይ ነው። በርካታ ክርስቲያኖች የበለጠ እግዚአብሔርን በታዘዝን ቁጥር የበለጠ እግዚአብሔርን እየወደድን እንሄዳለን እየተባሉ ሲማሩ ኖረዋል። ኢየሱስ ፍጹም ተቃራኒውን ነው የሚያስተምረው።

በክርስቶስ አነጋገር የበለጠ እግዚአብሔርን ስንወድ የበለጠ እግዚአብሔርን እንታዘዛለን። የግንኙነት መደነቃቀፎች ሲያጋጥሙ ኢየሱስ “በፍቅር ላይ አተኩሩ። ፍቅርን ተመልከቱ። እኔን ወደ መውደድ ተመለሱ። ችግሮቻችሁ የመነሣሳት ማጣት፣ እራስን መቆጣጠር ያለመቻል ወይም መንፈሳዊ እውነትን ለማወቅ ያለመቻል አይደሉም። ችግሮቻችሁ ፍቅርን ከማጣት የሚነሡ ናቸው።” ይላል። የመነሻው መስመር መታዘዝ ሳይሆን - ፍቅር ነው። እግዚአብሔርን ስንወድ ትእዛዘቱን እንጠብቃለን።

ፍቅራችን ሁል ጊዜ በመታዘዝ ይገለጣል፤ ነገር ግን የኛ መታዘዝ ሁል ጊዜ ፍቅርን ላያስከትል ይችላል።

በመንፈሳዊ ሕይወታችሁ በተደጋጋሚ የሚከሰቱት ሦስት ችግሮች ምንምን ናቸው?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ችግሩን ምላሽ የምንሰጥበት መንገድ በችግሩ ላይ ማተኮር አይደለም። ለችግሩ ምላሽ የምንሰጥበት መንገድ እግዚአብሔርን በመውደድ ላይ ማተኮር ነው።

በኢየሱስ ምሳሌዎች መሠረት ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት እንዴት ልናድግ እንችላለን? (ጥቆማ፤ ማርቆስ 1፥35፤ ዮሐንስ 14-15)

**የጸሎት ጥቆማ፤** “ጌታ ኢየሱስ ላውቅህ እፈልጋለሁ። ለመንፈሳዊነት የሚሆን ግልጽ አቅጣጫን እንዳይ ስለረዳኸኝ አመሰግንሃለሁ። በችግሮቼ ላይ ማተኮር ወደ መሸነፍ፤ በአንተ ላይ ማተኮር ወደ ድል እንደሚመራኝ አውቃለሁ። እንዴት ልወድህ እንደሚገባ አስተምረኝ። በኢየሱስ ስም ጸለይኩ። አሜን!”

**ለተጨማሪ ጥናት የሚሆኑ ምንባባት፤** ዘዳግም 6፥1-25፤ 30፥6፣ ኢያሱ 22፥5፣ 1ኛ ዮሐንስ 4፥16-21፤ ሮሜ 8፥12-17።

ማስታወሻ፤

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

## 6ኛ ቀን፥ ለምን እግዚአብሔርን በቤቴ ብቻ ማምለክ አልችልም?

ልማዱን ታውቁታላችሁ። ልክ እንደ ግብር ሊገመት የሚችል እና ደግሞም አስደሳች ነው። የእሁድ ማለዳ ዝብርቅርቅ ይባላል። የሚቀሰቅሳችሁን ደውል ይጮሃል፤ እናንተም ልክ በከባድ መኪና እንደተለተማችሁ ዓይነት ስሜት ይሰማችኋል። ልጆቹ በጥባጮች ናቸው፤ የሞቀ ውሃ የለም እና በሕጻናት ትምህርት ክፍል ውስጥ የምታሳልፉበት ሳምንታችሁ ነው፤ ውሻችሁ ደግሞ በምትወዱት ጫማችሁ ውስጥ ኩሱን ተቀማጭ አድርጎላችሁ ሄዷል። ሁሉ ነገር በተሳሳተ መንገድ እየሄደ ነበር። በዚህ ጊዜ ሁለት ጥያቄዎች ወደ አእምሮ ይመጣሉ "ሰንበታት ለምን በጣም አስቸጋሪ ቀናት ይሆናሉ፤ እናም ለምን አግዚአብሔርን በቤቴ አላመልክም?"

ታማኝ እንሁን እና ሁላችንም በመንፈሳዊ ሕይወታችን የሆነ ደረጃ ላይ ከእንደዚህ ዓይነት ጥያቄዎች ጋር ሙግት ውስጥ ገብተናል።

መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን አሳባችን እንዴት ነው ምላሽ የሚሰጠው? በሐዋርያት ሥራ 2፥42-47 ላይ ሉቃስ እነዚህን ቃላት ጽፏል፤

> በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም <u>ይተጉ</u> ነበር። ነገር ግን በሰው ሁሉ ፍርሀት ሆነ፤ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ድንቅና ምልክት ተደረገ። ያመኑትም ሁሉ <u>አብረው</u> ነበሩ፤ ያላቸውንም ሁሉ <u>አንድነት</u> አደረጉ። መሬታቸውንና ጥሪታቸውንም እየሸጡ፥ ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉት ነበር። በየቀኑም <u>በአንድ ልብ</u> ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ፥ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፤ እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።

ለክርስቲያኖች የነበረውን ልማድ ለማሳየት የተወሰኑ ቃላት ላይ እስምሬባቸዋለሁ። የተሰመረባቸው ቃላት ብዙ ቁጥርን የሚያመለክቱ ወይም በሆነ መንገድ ቡድናዊ የሆኑ ናቸው። እዚህጋ አሳቡ ግልጽ ነው። ከኅብረት የተለየ ምንም ዓይነት ክርስትና የለም። እግዚአብሔን ለምን በቤቴ ሆኜ አላመልክም? መልሱ አግዚአብሔር የክርስትና ሕይወትን ያበጀው/የቀረጸው ሙሉ በሙሉ በአማኞች ኅብረት ውስጥ እንዲገለጥ እና ደስ የሚያሰኝ እንዲሆን ነው።

የመጀመሪው ክፍለ ዘመን ቤተ ክርስቲያን በጋራ ያጠኑ ነበር፤ አብረው ይወጡና ይገቡ ነበር፤ አብረው ይመገቡ ነበር፤ አብረው ይጸልዩ ነበር፤ አብረው ሕይወትን ይለማመዱ ነበር፤ ያላቸውን አንድ ላይ አድርገው ነበር፤ አብረው የጌታን እራት ይወስዱ ነበር፤ ከሁሉም በላቀም አብረው ያመልኩ ነበር። ክርስትና የቡድን ስፖርት ነው!

ለእግዚአብሔር ፍቅራችንን የምንገልጽበት ከታላቅ አማራጮች አንዱ በኅብረት አምልኮ ዐውድ ውስጥ ነው። በአንድ ድምጽ እርሱን እናመሰግናለን! በአንድ ልብ እርሱን እንፈልጋለን። በአንድ አሳብ እርሱን ልናውቀው እንጠማለን። እንደ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አካል አብዛኛው በክርስቶስ ማደጋችን እና ለክርስቶስ ያለን ጥማት የሚወሰነው ከአካሉ ጋር ባለን መያያዝ ነው።

ዛሬ የጋራ አምልኮን የሳምንት ሥራችሁ መደበኛ አካል ልታደርጉ ወስኑ!

ለመጀመሪያው ክፍለ ዘመኗ ቤተ ክርስቲያን በመደበኛነት "በቤተ መቅደስ" እና "ቤት ለቤት" መሰብሰብ አስፈላጊ የሆነው ለምን ይመስላችኋል?

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**የጸሎት ጥቆማ፤** ጌታ ኢየሱስ ላውቅህ እፈልጋለሁ። በአንተ የማደግ ሂደቴ አንዱ ክፍል ከሌሎች አማኞች ጋር ባለኝ መያያዝ እንደሚገኝ ተረድቻለሁ። በኅብረት አምልኮ ውስጥ ስለመካፈል ዕድል አመሰግንሃለሁ። እባክህን ከሌሎች ጋር ሆኜ እንድከተልህ እርዳኝ። በኢየሱስ ስም ጸለይኩ። አሜን!"

**ለተጨማሪ ጥናት የሚሆኑ ምንባባት፤** ዕብራውያን 10፡23-25፤ ቆላስይስ 3፥12-16።

ማስታወሻ፤

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------


--------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------



## ሳምንት ሁለት

# ከአማኞች ጋር አንድ መሆን

## 1ኛ ቀን፥ የመበረታቻ ስፍራ

በሚያበረታቱ ሰዎች መካከል መገኘትን አትወዱም? ስለ ጫማችሁ፣ ስለ ጸጉራችሁ፣ ስለ ችሎታዎቻችሁ እና ጥንካሬዎቻችሁ ብሎም እነሱ ስላስተዋሉትን ማንኛውም ነገር አስተያየት ይሰጧችኋል። እነርሱ ትክክለኛውን ነገር በትክክለኛው ሰዓት እና በትክክለኛው መንገድ ለመንገር ብቃት አላቸው። ያም ከፍ ብላችሁ እንድትሄዱ እና በተስፋ እንድትሞሉ ያደርጋችኋል። በተመሳሳይ መንገዶች ማበረታታት ለተጎዱ ሰዎች የቃል መታሻ ነው።

በቅርብ ሳምንታት አዲስ ኪዳንን እያነበብኩ እያለ አንድ አሳብን የሚገዛ ልማድ አስተዋልኩ። ሐዋርያቱ አብዛኛውን አገልግሎታቸውን የሚያሳልፉት አማኞችን በማጠናከር እና ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው አካሄድ ላይ በማበረታታት ነው። ማበረታታት እና ጥንካሬ እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚሄዱ ነገሮች ናቸው። ከዚህ ቀጥሎ የተሰጡትን ምሳሌዎች ተመልከቱ፡

- "ባነበቡትም ጊዜ ከምክሩ የተነሣ ደስ አላቸው።" (በይሁዳ እና በሲላስ የተወሰደ/የተላከ ደብዳቤ) (የሐዋርያት ሥራ 15፥31)
- "ይሁዳና ሲላስም ... ወንድሞችን በብዙ ቃል መከረው አጸኑአቸው።" (የሓዋርያት ሥራ 15፥32)
- ". . . ወንድሞችንም ባዩ ጊዜ አጽናኑአቸውና ሄዱ።" (የሓዋርያት ሥራ 16፥40)
- "ስለዚህ እናንተ ደግሞ እንደምታደርጉ፥ እርስ በርሳችሁ ተመካከሩ አንዱም አንዱም ሌላውን ያንጸው።" (1ኛ ተሰሎንቄ 5፥11)
- "ኢዮስጦስም የተባለ ኢያሱ . . . በእግዚአብሔር መንግሥት ከእኔ ጋር አብረው የሚሠሩት እነዚህ ብቻ ናቸው፥ እኔንም አጽናንተውኛል።" (ቆላስይስ 4፥11)
- "የደቀ መዛሙርትን ልብ እያጸኑ በሃይማኖትም ጸንተው እንዲኖሩ እየመከሩና፡ 'ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል' እያሉ፥ . . ." (የሐዋርያት ሥራ 14፥22)
- "ነገር ግን ከእናንተ ማንም በኃጢአት መታለል እልከኛ እንዳይሆን፥ ዛሬ ተብሎ ሲጠራ ሳለ፥ በእያንዳንዱ ቀን እርስ በርሳችሁ ተመካከሩ፤" (ዕብራውያን 3፥13)

እኔ ሁል ጊዜ የአነስተኛ የጥናት ቡድኖች ዓላማ ጠለቅ ያለ ትምህርት ማካሄድ ነው ተብዬ ተምሬአለሁ። ይሄ አንዱ ክፍል ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ከአማኞ ጋር አንድ መሆን መረጃን ከማግኘት ያለፈ ሲሆን እና ስለማበረታታት እና ስለማጽናናት ሲሆንስ? ሁላችንም መጽሐፍ ቅዱስን ተግባራዊ ከምናደርገው በላይ እናውቀዋለን፤ ነገር ግን ማናቸውም ሰው ከሚያስፈልጋቸው በላይ ማበረታቻ አግኝተው አያውቁም!

በሚያስከፉ ሁኔታዎች ውስጥ እያለፋችሁ ነውን? ከሆነ እራሳችሁን ሁለተኛውን ጥያቄ ጠይቁ፤ "ሰዎች ለእኔ ማበረታቻ እና ሕይወቴን የሚያጸኑ ነገሮች ወደሚናገሩበት ስፍራ እራሴን ወስጃለሁን?"

እናንተ አሁን በአነስተኛ ቡድን ውስጥ የማትሳተፉ ከሆነ ወደ ኋላ እየጎተታችሁ ያለው ምንድን ነው?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ከእነዚህ ጉዳዮች መካከል የትኛውንም ቢሆን በጸሎት ወደ እግዚአብሔ አቅርባችሁ ታውቃላችሁን? ካልሆነ ግድ የሚላችሁን ጉዳይ ለእግዚአብሔር አካፍሉ።

ዕብራውያን 10፥23-25 በጋራ ስለመሰባሰብ ምን ያስተምረናል?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**የጸሎት ጥቆማ፤** “ጌታ ኢየሱስ ላውቅህ እፈልጋለሁ። ማበረታቻ እና ጥንካሬ በኅብረት ውስጥ ከሌሎች አማኞች ጋር በመሆን እንደሚገኙ ተረድቻለሁ። ከሌሎች ጋር ስገናኝ እራስህን ለኔ እና በኔ በኩል ግለጥ። በኢየሱ ስም ጸለይኩ፤ አሜን!”

**ለተጨማሪ ጥናት የሚሆኑ ምንባባት፤** የሐዋርያት ሥራ 11፥19-24፤ ቆላስይስ 3፥15፤ 1ኛ ተሰሎንቄ 5፥11-14።

ማስታወሻ፤

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

## 2ኛ ቀን፥ ሰዋዊ ገጽታ

በክርስቲያኖች መካከል ስለመንፈሳዊ እድገት ብዙ ይወራል። እድገት አስፈላጊ እንደሆነ እና ማደግ አለማቻል የሚያደርቅ እንደሆነ እናውቃለን። ነገር ግን አጠቃላይ ታሪኩ ተነግሮን አውቀነዋልን?

ወደ አካባቢያችሁ የክርስቲያን መጻሕፍት መደብር ብትሄዱ በእምነት ማደግ እንድትችሉ ሊረዷችሁ (እንዲሳድጓችሁ) በተጻፉ መጻሕፍት ዓይኖቻችሁ ይጥበረበራሉ። በጸሎት ኃይል ዙሪያ የተጻፉ መጻሕፍትንም ልታነቡ ትችላላችሁ። ለጥሞና ሕይወት የሚሆኑ በርካታ ስልቶችንም ልታጠኑ ትችላላችሁ። በመንፈሳዊ ስጦታዎች ዙሪያም የበቃ አዋቂ ልትሆኑ ትችላላችሁ። ነገር ግን በምታነቡት እያንዳንዱ መጽሐፍ የሚፈነጠቀው እና ቋሚ የተለመደው መልዕክት “ዕድገት ሊመጣ አንድ መጽሐፍ ብቻ ማንበብ ቀርቶዎታል!” የሚል ነው።

ወይስ እውነት ነውን?

በእናተ ልምድ ስንት እራሳቸውን በራሳቸው ያስተማሩ ደቀ መዛሙርት አጋጠሟችሁ? መጻሕፍት የግል ዕድገት አካል መሆናቸው እንዳለ ሆኖ የክርስትና ሕይወት “የተሟላ (ብቸኛ) የማጥኛ ዘዴ” እንዲሆኑ የሚታሰቡ አይደሉም። መጻሕፍት እውነታዎችን ከተደበቁበት ሊገልጡ እና መረዳታችንን ሊያሰፉ ይችላሉ፤ ነገር ግን የሰው ለሰው ምልልስን ቦታ ሊወስዱ አይችሉም። ምሳሌ 27፥17 “ብረት ብረትን ይስለዋል፥ ሰውም ባልንጀራውን ይስላል።” በእግዚአብሔር እቅድ የእድገታችን ዋናው ክፍል የሚገኘው ከሌሎች አማኞ ጋር በሚኖረን ግንኙነት እና የአሳብ ልውውጥ ውስጥ ነው።

ለመንፈሳዊ እድገት በእግዚአብሔር የተመረጡት መሣሪያዎች መጻሕፍት (አማኞች መሆናቸው ቀርቶ) ቢሆኑ ኖሮ መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት በተለየ መንገድ ሊነበብ እንደሚችል አስቡት? የተወሰኑ ክለሳዎች ምናልባት ያስፈልጉን ይሆናል፡

- “መጻሕፍት አእምሮን እንደሚስሉ አንድ መጽሐፍ የሚያነቡትን ይስላል።” (አዲሱ ምሳሌ 27፥17)
- “ያመኑትም ሁሉ እያነበቡ በቤታቸው ነበሩ፤ በጋራ ያላቸው ነገርም ጥቂት ብቻ ነበር። (የሚገናኙት በጣም አልፎ አልፎ ስለነበር) ነገር ግን ማንኛውም እንደሚፈልግ መጻሕፍትን እና ማስወሻዎችን በመለዋወጥ ፥ ከሁሉም ጋርም ቢጋሮችን በመከፋፈል ያሳልፉ ነበር።” (አዲሱ የሐዋርያት ሥራ 2፥44-45)
- “የበለጠ መረጃ አላቸውና አንድ መጽሐፍ ብቻ ከመሆን ሁለት መጻሕፍት ይሻላሉ።” (አዲሱ መክብብ 4፥9)

መጻሕፍት ታላቅ ነገሮች ናቸው፤ ነገር ግን በመንፈሳዊ እድገት ላይ ሰዋዊ ገጽታን ሊተኩ አይችሉም።

ከአማኞች ጋር ኅብረት ማድረግ ለመበረታታት እና ለመተናነጽ አስፈላጊ እንደሆነ እናውቃለን። ዛሬ ከአማኞች ጋር ኅብረት ማድረግ ለመንፈሳዊ እድገት ቁልፍ እንደሆነ ልናይ እንችላለን። ለመንፈሳዊ እድገታችሁ ዓላማ ከማን ጋር ነው በመደበኛነት እየተገናኛችሁ ያላችሁት?

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

የኛ መንፈሳዊ እድገት አንዱ ክፍል ከሌሎች ጋር ኅብረት በማድረግ የሚመጣ ከሆነ ያ ማለት የሌላ የአንድ ሰው መንፈሳዊ እድገት ከፊል ከእናንተ ጋር በመገናኘት የሚመጣ ነው ማለት ነው። ለሌሎች ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል እግዚአብሔር ያስተማራችሁን ሁለት ጉዳዮች ዘርዝሩ፤ (ለምሳሌ፥ ጸሎት፣ እምነት፣ ትዕግስት፣ ለሌሎች ግድ መሰኘት፣ ወዘተ . . . )።

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**የጸሎት ጥቆማ፤** "ጌታ ኢየሱስ ላውቅህ እፈልጋለሁ። የእድገቴ ከፊል ክፍል ከሌሎች ጋር ኅብረት በማድረግ እንደሚመጣ አውቄያለሁ። የእኔን መርሐ ግብር እና በሕይወቴ ያለኝን ስፍራ ከሚመጥኑ ቡድኖች ጋር በማገናኘት ልትረዳኝ ትችላለህን? ስለእያንዳንዷ የዕድገት ሂደቴ ክፍል ስለምትጠነቀቅልኝ አመሰግንሃለሁ። እወድሃለሁ! በኢየሱስ ስም ጸለይኩ። አሜን!"

**ለተጨማሪ ጥናት የሚሆኑ ምንባባት፤** ሮሜ 12፥1-13፤ ኤፌሶን 4፥1-16፤ 1ኛ ተሰሎንቄ 3፥11-13።

ማስታወሻ፡

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

## 3ኛ ቀን፥ ለስግብግብነት ሕይወት የቀረበ ተግዳሮት

*“ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ፥ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር፤ እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፥ ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ።”* - ፊልጵስዩስ 2፥3-4

እዚህ ጋ ያለው ታሪክ በአጠቃላይ ስለእናንተ ብቻ አይደለም። ለመቀበል የሚከብድ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ነገሩ ግን እውነት ነው! አብዛኞቻችን ሕይወት አንድ ትልቅ ታሪክ ነች ብለን ለማሰብ እንፈተናለን፤ እናም እኛ ማዕከላዊ የሆነ ሚና አለን። የሚከናወን ማንኛውም ነገር ለእኛ እንደ ተግዳሮት፣ የመረማመጃ ድንጋይ ወይም ትምህርት ማግኛ ሆኖ ይታያል። የቀደመ እምነታችንን ፈጽሞ በዚህ መልኩ በቃል አናስቀምጥ ይሆናል ነገር ግን አምልጠውን የሚወጡ አሳቦች ያጋልጡናል፤

- *እግዚአብሔር ሆይ፥ ሂሳቤ ወርዷል። ለምን ሁልጊዜ እነዚህ ነገሮች እንዲደርሱብኝ ትፈቅዳለህ?*
- *እግዚአብሔር ሆይ፥ በቂ ገንዘብ የለም። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ልታስተምረኝ የምትፈልገው ምንድን ነው?*
- *እግዚአብሔ ሆይ፥ እንደገና አምሽቼ መሥራት ይገባኛል። ለምንድነው እኔ ብቻ ተደራራቢ ሥራ ለመሥራት የምገደደው?*

የእኛ የሕይወታችን ተደጋጋሚ ገጠመኞች የሚመጡበት የላቀ ዓላማ ከእኛ አንጻር ምንም የማይፈይድልን ቢሆንስ? ያለው የገንዘብ መጠን ለአንድ ሰው ጠቃሚ ስላልሆነ ቢወሰድስ? እግዚአብሔር የአንድ ሰው ጸሎት ለመመለስ የእናንተን አንዳንድ ነገሮች ቢወሰድስ? የእናንተ አምሽቶ የመሥራት ችሎታ (ብቁ መሆን) አግዚአብሔርን የአንድ ሰውን የትዳር ችግር ለመፍታት እንዲችል የሚያመቻቸው ቢሆንስ? በዙሪያችን አንድ ትልቅ ክስተት ቢገለጥም ነገር ግን የሚሆነው እያንዳንዱ ነገር ስለእኛ ብቻ የሚሆን አይደለም።

በእያንዳንዱ አማኝ ሕይወት የሚከተለውን ጥያቄ የሚመልሱበት ምዕራፍ አለ፤ ሕይወቴን ለራሴ ነው መኖር ያለብኝ ወይስ ለሌሎች አሳልፌ መስጠት አለብኝ? ኢየሱስ ሕይወቱን ሊያድን የሚወድ ያጠፋታል፤ ሕይወቱን የሚሰጥ ግን ያገኛታል። ብሎ አስተምሯል፤ (ማቴዎስ 16፥25)።

ከአማኞች ጋር ኅብረት የማድረግ በረከቶች መካከል አንዱ ስለሌሎች እንድናስብ ማስገደዱ ነው። በተፈጥሮ ስለሌሎች አስፈልጎት (ጉድለት) የምራቸውን ግድ የሚላቸው በጣም ጥቂት ሰዎች አሉ። በሰው ልጅ ውድቀት የተነሣ የእኛ ተፈጥሮአዊ ማንነታችን ዝንባሌ ተስፋ በሚያስቆርጥ ሁኔታ በራስ ላይ ያተኮረ ነው። እራስን መካድ እና ሌሎችን ማገልገል ክርስቶስን ለመምሰል የሚደረገው ጉዞ አንድ አካል ነው፤ (ማቴዎስ 16፥24-27)። በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ማኅበረሰብ ውስጥ አማኞች ሲሰባሰቡ እነዚህ ሁለቱም ምላሽ ያገኛሉ።

የምናከናውነው ነገር ታሪክ በአጠቃላይ ስለእኛ አለመሆኑን እውቅና ለመስጠት አዳጋች የሚሆንብን ለምንድን ነው?

--------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------

እኛ በአነስተኛ ቡድኖች ኅብረት ውስጥ በምንመጣበት ጊዜ ለመርዳት፣ ለማገልገል፣ ለመበረታታት እና እርስ በእርስ ለመተናነጽ ዓላማ ስንመጣ ቡድኑ እንዴት ነው የተለየ ሊሆን የሚችለው?

--------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------

**የጸሎት ጥቆማ፤** "ጌታ ኢየሱስ ላውቅህ እሻለሁ። በሚደረገው ነገር ታሪክ ውስጥ ማዕከላዊውን ስፍራ ለመያዝ ስለመመኘቴ ንስሃ እገባለሁ፤ ብሎም ውስጤንም ውጪዬንም ሳይቀር እንድትለውጠኝ እሻለሁ። ባለኝ እውቀት ሁሉ በተቻለኝ እራሴን ለአንተ አስገዛለሁ፤ እናም ሌሎችን ለመባረክ ዓላማ በእኔ ውስጥ እንድትኖር እለምንሃለሁ። በኢየሱስ ስም ጸለይኩ። አሜን!"

**ለተጨማሪ ጥናት የሚሆኑ ምንባባት፤** ፊልጵስዩስ 2፥1-11፤ ገላትያ 6፥1-2፤ ቆላስይስ 3፥12-17።

ማስታወሻ፡

--------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

## 4ኛ ቀን፥ ከክብደት ማንሻ ክፍል የሚገኙ ትምህርቶች

ስድስተኛ ክፍል እያለሁ ወደ ክብደት ማንሻ ክፍል በመሄድ በዛ ያለውን አስደናቂ ነገር የማውቅበት ዕድል አግኝቼ ነበር። ወዲያውኑ የጂም ሕይወት በራሱ በአንድ ባህል ውስጥ ያለ የተለየ ባህል መሆኑን በፍጥነት ተረዳሁ። ሰዎቹም የተለዩ ሰዎች ናቸው። የሚያስቡት እና የሚንቀሳቀሱት በተለየ መንገድ ሆኖ የሚለብሷቸውን ልብሶች ሳይቀር ለአብዛኞቻችን እንግዳ ናቸው። ጣት የሌላቸው ጓንቶች አሉ፣ እጅጌ የሌላቸው ሸሚዞች እና ምንም ድብቅ ነገር የማያስቀሩ ሱሪዎች ይለበሳሉ። በዚያ ስፍራ እጥረት የሌለበት ብቸኛ ነገር ትዕቢት ነው!

ያለ ምንም ጥርጥር በክፍሉ ውስጥ የሚኖረው ትንሹ ሰው ከሁሉም የበለጠ ሊያወራ እና የበለጠ ጫጫ ሊሆን፥ ሆኖም ከሁሉም ያነሰ ክብደት የሚያነሳ ሊሆን ይችላል። ለአምስት ደቂቃ ቆየት ብላችሁ ብታዩ በቂ ልምድ ያዳበሩትን እና በቂ ልምድ እንዳላቸው ሊያሳዩዋችሁን የሚፈልጉትን በቀላሉ ትለዩዋቸዋላችሁ።

ልምድ ያካበቱት ደህና ልብሶችን ይለብሳሉ በሚሠሩበት ጊዜ ሁሉ እራሳቸውን በተወሰነ መጠን ያሠራሉ፤ ብሎም ከበድ ያለ ክብደት ሲያነሡ ደራሽ ሰው አጠገባቸው እንዲኖር ያደርጋሉ። ልምድ የሌላቸው ደግሞ ያሉትን አልባሳት በሙሉ ይለብሳሉ፤ ችሎታቸውን በሚነሳው ክብደት በሙሉ ይፈትናሉ፤ እናም ደራሽ ሰው ማቆምን እንደ ደካማነት ምልክት አድርገው ይወስዳሉ። የዘነጠ ጓንት ካጠለቀ፣ እጅጌ የሌለው ሸሚዝ ከለበሰ እና ጥብቅ ያለ ሱሪ ካደረገ ሰው ደረት ላይ ወድቆበት የተጫነውን ክብደት ምን ያህል ጊዜ እንዳነሳሁ ልነግራችሁ አልችልም። (ይህ በጣም ጥሩ ገጽታ አይደለም።)

ብታምኑም ባታምኑም ካነሳነው የጂም ገጽታ ልናወጣ የምንችላቸው አንድ ሁለት መንፈሳዊ እውነታዎች አሉ። 1ኛ፡ ልምድ እራሱን በጥበባዊ ውሳኔዎች ይገልጻል። 2ኛ፡ ልምድ እገዛ ለመጠየቅ አይፈራም። ሰሎሞን እንዲህ አለ፤

> *"ድካማቸው መልካም ዋጋ አለውና አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል። ቢወድቁ አንዱ ሁለተኛውን ያነሣዋልና አንዱ ብቻውን ሆኖ በወደቀ ጊዜ ግን የሚያነሣው ሁለተኛ የለውምና ወዮለት።"* (መክብብ 4፥9-10)።

ከእግዚአብሔር ጋር መሄድን የተለማመዱ በሳል አማኞች በቋሚነት ጥበበኛ ውሳኔ ይወስናሉ። ሆነ ብለው በአማኞች ድጋፍ ማግኛ ሁኔታ ውስጥ ራሳቸውን ያስገባሉ ምክንያቱም "አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል።" በየመታጠፊያው ላይ ቆም እያሉ ብቁ እንደሆኑ እራሳቸውን ማሳየት አያስፈልጋቸውም። ስለሆነም የቀረበላቸውን እድል ሁሉ ይጠቀማሉ። (ለምሳሌ፡- የአምልኮ አገልግሎት፣ አነስተኛ ቡድኖች፣ የየዕለቱን ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር፣ የአገልግሎት ኃላፊነቶችን፣ ተጠያቂ በሚሆኑላቸው ቡድኖች ዘንድ፣ ወዘተ፥)። በሳል አማኝ በእነዚህ አካባቢዎች የሚቀርቡትን በርካቶቹን መረጃዎች ሊያውቅ ቢችልም ስለተጠያቂነት እና ስለማኅበረሰቡም ያለባቸውን አስፈልጎትም እንዲሁ ይለዩታል። መቼ እንደሚወድቁ ያውቃል፤ እናም ሌላ የሚያነሣ ሰው ማግኘት መልካም ነው።

ወጣት እና ገና ያልበሰሉ አማኞች በስሕተት መሣሪያዎችን የመንፈሳዊነት ምልክት አድርገው ይወስዳሉ። ትክክለኛ መሣሪያዎች በሙሉ አሏቸው፤ ነገር ግን ያላቸውን ነገር እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው አያውቁም። እራሳቸውን ጊዜው እንደሌላቸው ወይም የነገሩ አስፈላጊነት አስቸኳይ አይደለም ብለው በማሳመን ለመደበኛ እድገት የሚሆኑ እድሎችን ያሳልፋሉ። ከሌሎች አማኞች ጋር አብረው ሲሆኑ እራሳቸውን መንፈሳዊ ሲያስመስሉ እና በሁሉም አቅጣጫ እራሳቸውን የማስመስከርን አስፈላጊነት ላማሳየት ሲታገሉ ያገኙታል። ያለጥርጥር ያላቸውን አቅም ሁሉ አሟጠው ይጠቀማሉ፤ ብሎም ትዕቢት እርዳታ ከመጠየቅ ያግዳቸዋል። ሲወድቁም እራሳቸውን በመለየት ወይም በማራቅ ውስጥ ያስገባሉ።

የክርስትና ሕይወት የአጭር ርቀት ሩጫ አይደለም፤ ማራቶን ነው! ማንም ብቻውን አያካሂደውም፤ ቋሚ እና ጥበብ የሞላቸው ውሳኔዎች አልፎ አልፎ ከሚከሰቱ የመንፈሳዊነት ብልጭታዎች ወይም ርችቶች የበለጠ ይሠራሉ።

ቲቶ 2፥3-6፤ ሮሜ 12፥10 እና ዕብራውያን 11፥1-12፥2 አንብቡ።

**የጸሎት ጥቆማ፤** “ጌታ ኢየሱስ ላውቅህ እሻለሁ። አንተን ላውቅ የምችልበት አንዱ መንገድ ለረጅም ጊዜ አንተን ያወቁትን ሰዎች ሕይወት በመመልከት እንደሆነ ተረድቻለሁ። የበሰሉ አማኞች የሚገኙበት ዐውድ ውስጥ ሕይወቴን ለማስገባት ቁርጠኛ እሆናለሁ። በኢየሱስ ስም ጸለይኩ። አሜን!”

ማስታወሻ፤

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

# 5ኛ ቀን፥ የማኅበረሰብ የሕይወት ዘይቤ የምርጫ ጉዳይ ነው

ባለፉት አራት ቀናት ከአማኞች ጋር ኅብረት ማድረግ ማበረታቻ ለማቅረብ እና ለመተናነጽ፣ ለግል እድገት የሚጠቅም አካባቢ ለመመስረት፤ የስግብግብነት አኗኗርን ለመገዳደር፣ እና ከማኅበረሰብ ደህንትነት አንጻር ጥበብ የሞላባቸው ውሳኔዎችን ለመወሰን ጠቃሚ መሆኑን አይተናል። ዛሬ ከአማኞች ጋር ኅብረት ማድረግ ለመረጡት እንዴት ሐሴትን የሚሰጥ የሕይወት ዘይቤ ምርጫ መሆኑን እንመለከታለን።

በሐዋርያት ሥራ 2፥42-47 ሉቃስ ሲጽፍ፡

> "በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር። ነገር ግን በሰው ሁሉ ፍርሀት ሆነ፤ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ድንቅና ምልክት ተደረገ። ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ፤ ያላቸውንም ሁሉ አንድነት አደረጉ። መሬታቸውንና ጥሪታቸውንም እየሸጡ፥ ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉት ነበር። በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ፥ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፤ እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።"

እንዴት አስደናቂ የአማኞች ስብስብ ነው! ስለ የሕይወት ዘይቤ ምርጫዎች ብዙ እንሰማለን። ከሰንበት ትምህርት ቤት እስከ ሕዝብ ጤና ማስታወቂያዎች ጥበብ የተሞላ ውሳኔ እንድንወስን እንሞገታለን። ዓላማው የምናደርጋቸው የሕይወት ዘይቤ ምርጫዎች የምንኖረውን ሕይወት ምንነት እንደሚወስኑ ሌሎች ሰዎች እንዲመለከቱ ለማስቻል ነው።

እኔ ስለ ሕይወት ዘይቤ ምርጫዎች ስናገር አጠቃላዩን የሕይወታችሁን ፍሰት እና ሂደት የሚይዙትን ውሳኔዎች ማለቴ ነው። ለምሳሌ:- ሃሺሽ የመውሰድ፣ ዕጻን የማምጣት፣ ወይም ወደ ኮሌጅ የመግባት ውሳኔዎች የሕይወታችሁን አጠቃላይ ፍሰትም ሆነ ሂደት ይወስናሉ። ኢየሱስን ለመከተል፣ የተዋጣለት የእግር ኳስ ተጫዋች ለመሆን፣ ወይም ንግድ ለመጀመር መወሰንም እንዲሁ የሕይወታችሁን ፍሰት እና ሂደት ይወስናሉ። የሕይወት ዘይቤ ምርጫዎች ጥሩም መጥፎም ሊሆኑ ይችላሉ። ብሎም ሁሉም የሕይወት ዘይቤ ምርጫዎች ተመሳሳይ ተጽእኖ ባይኖራቸውም ነገር ግን ቀን በቀን የምትኖሩበትን አኗኗር ይለውጡታል።

ሕይወትን በጋራ መኖር የሕይወት ዘይቤ ምርጫ ነው። አማኞች ከተለመደው ቤተ ክርስቲያን የመሄድ ድግግሞሽ እና የአልፎ አልፎ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ባለፈ ጠለቅ ባለ ደረጃ አንድ ሊሆኑ ሲመርጡ ያ አጠቃላዩን የሕይወታቸውን ፍሰት እና ሂደት ይለውጣል። የመጀመሪው ክፍለ ዘመን ቤተ ክርስቲያን በጋራ ይማሩ፣ ሕብረት ያደርጉ፣ ይመገቡ፣ እና ይጸልዩ ነበር። በማኅበረሰብ ዐውድ ውስጥ በመደበኛነት የእግዚአብሔርን አብሮነት ይለማመዱ የነበረ ሲሆን የእግዚአብሔር እጅግ ታላቅ ኃይልም ይመለከቱ ነበር። ብዙ የጋራ ነገሮች ነበሯቸው፤ ብሎም እርስ በእርሳቸው በመስጠት እና በመካፈል ይተጋገዙ ነበር። ልባቸው ለምስጋና የተሰበረ እና በየዕለቱም ሰዎች በእነርሱ ላይ ሲጨመሩላቸው የሚያዩ ነበሩ። እንዴት አስደናቂ ገጽታ ነው። <u>ነገር ግን</u> . . . በቀኑ መጨረሻ

በሕብረት ለመሆን ያደረጉት ምርጫ በጥቅሉ የኖሩትን ኑሮ የሚወስነው ነበር። መቼም ኅብረትን በዚያ ደረጃ እንድትለማመዱት አትገደዱም። ነገር ግን የእውነተኛ ኅብረት አሳብ እና ናፍቆት ይህንን የማኅበረ ሰብ ሕይወት ዘይቤ እንድትመርጡት ያደፋፍራችኋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

ስለ እውነተኛ ኅብረት ስጋቶች አሏችሁን? ከታች ዘርዝሯቸው?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**የጸሎት ጥቆማ፤** "ጌታ ኢየሱስ ላውቅህ እሻለሁ። እኔ ልሆንበት የሚገባኝን ስፍራ ስለሰጠኸኝ አመሰግንሃለሁ። ስለ እግዚአብሔር ቤተሰብም አመሰግንሃለሁ። ስለማኅበረሰብ/ኅብረት ሊኖረኝ የሚችለውን ፍርሃት ሁሉ አልፌ መሄድ እንድችል እርዳኝ፤ እናም ከሌሎች አማኞች ጋር የጠለቀ ግንኙነትን እንድጠማ አግዘኝ። በኢየሱስ ስም ጸለይኩ። አሜን!"

**ለተጨማሪ ጥናት የሚሆኑ ምንባባት፤** የሐዋርያት ሥራ 4፥32-35፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 12፥4-27፣ ኤፌሶን 4፥1-6።

ማስታወሻ፡

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

# 6ኛ ቀን፥ እንዳችን ሌላችንን ማገልገል

የክርስቶስ ኢየሱስ ደቀመዝሙር መሆን ማለት ምን ማለት ነው? ደቀ መዝሙርን ስናስብ ሁል ጊዜ የሚመጣብን ተማሪ ነው (ከመምህሩ የሚማር የሆነ ሰው)። የመማር ነገር በእርግጥ መኖሩ እንዳለ ሆኖ ደቀ መዝሙ ግን ከተማሪነት ብቻ ያለፈ ነው። የክርስቶስ ደቀ መዝሙር ክርስቶስን ለመምሰል ኢየሱስ ያደረገውን የሚያደርግ ሰው ነው። ይህንን አሳብ ውሰዱ እና ደቀ መዛሙርትን ወደማፍራት ዐውድ አምጡት። እንደ ቤተ ክርስቲያን የእኛ ግብ ደቀ መዛሙርት ማድረግ ነው። ስለዚህ በደቀ መዝሙር ማድረግ ላይ ያለ ማንኛውም ውይይት ክርስቶስ እንደኖረው የመኖርን ውይይት የሚያካትት ነው። በማቴዎስ 20፥26-28 ላይ ኢየሱስ እንዴት እንደኖረ ጠቃሚ እውነታን አካፍሏል።

> "በእናንተስ እንዲህ አይደለም፤ ነገር ግን ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን፥ ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የእናንተ ባሪያ ይሁን፤ እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።"

ኢየሱስ ሌሎችን ሊያገለግል መጣ! እንደ ክርስቲያን በኢየሱስ ትምህርቶች፣ ተአምራት ወይም መለኮታዊ አሠራሮች ላይ ማተኮር ቀላል ነው። ነገር ግን ዕለት በዕለት የኖረውን የኢየሱስን አኗኗር ለመረዳት ከፈለግን የአገልግሎት ሕይወቱን ማየታችን የግድ ነው።

ይሄ ለኛ ምን ትርጉም ይሰጠናል? ሌሎችን ማገልገል የሕይወታቸን ዋና ክፍል ሊሆን እንደሚገባ ያስተምረናል። እንዴት ማገልገል እንዳለብን የምንማርበት ከመጀመሪያዎቹ አንዱ የሆነው አካባቢ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ዐውድ ነው። አንዳችን አንዳችንን በማገልገል እንማራለን። ለዚህ ዓላማ ነው መንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ለእያንዳንዱ አማኝ የሰጠው። 1ኛ ቆሮንቶስ 12፥7 "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል።" ይለናል። "ለእያንዳንዱ" የሚለው ቃል ላይ ትኩረት ስጡ። ሁላችንም መንፈሳዊ ስጦታ አለን። እናም እግዚአብሔር እያንዳንዳችን ያንን ስጦታ ሌሎችን ለማገልገል ዓላማ እንድናውለው ይፈልጋል።

ከሌሎች አማኞች ጋር በጋራ አንድ ስንሆን በአካሉ ውስጥ ያሉትን አስፈልጎቶች ምንነት እናውቃለን። አስፈልጎቶቹ ሲታወቁ የየራሳችንን መንፈሳዊ ስጦታዎች እግዚአብሔር ባቀደው አቅጣጫ የመጠቀም ዕድልን ይሰጠናል። ስናገለግል የክርስቶስን ሕይወት ምሳሌ እናደርጋለን። በመጨረሻም የክርስቶስን ሕይወት ምሳሌ ስናደርግ እኛ የእውነት የእርሱ ደቀ መዛሙርት ነን ማለት ነው።

መንፈሳዊ ስጦታ(ዎቻ)ችሁን ታውቃላችሁ? የምታውቁ ከሆነ ጻፏቸው። ካልሆነም ለመፈለግ ፈቃደኛ ናችሁን?

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ከሌሎች አማኞች ጋር ኅብረት ስታደርጉ የምትመጡት ልታገለገሉ ነው ወይስ ልትገለገሉ? የክርስቶስን አካል በሙሉ ዓቅማችሁ እያገለገላችሁ እንዳላችሁ ታምናላችሁ? ምን ያህል ልታለግሉ ትችላላችሁ?

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

የጸሎት ጥቆማ፤ "ጌታ ኢየሱስ ላውቅህ እሻለሁ። ሌሎችን ለማገልገል እንድጠቀምበት መንፈሳዊ ስጦታ ስለሰጠኸኝ አመሰግናለሁ። ባለኝ አቅም ልክ እንድትጠቀምብኝ እጸልያለሁ። ስጦታዎቼን ከሌሎች ጋር ለመከፋፈል ድፍረት ስጠኝ። በኢየሱስ ስም ጸለይኩ፤ አሜን!"

**ለተጨማሪ ጥናት የሚሆኑ ምንባባት፤** ሮሜ 12፥4-9፣ 1ኛ ጴጥሮስ 4፥10-11፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 12።

ማስታወሻ፤

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------



## ሳምንት ሦስት

# ዓለምን አገልግሉ።

## 1ኛ ቀን፥ መልካሙን ሥራችሁን እንዲያዩ

*"መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ።"* ማቴዎስ 5፥16

በክርስቶስ ሆኜ ከተለወጥኩ ጥቂት ጊዜ በኋላ ቦብ የሚባል አንድ ግዙፍ የሰው ፍጡር ተዋውቄ ነበር። ቦብ 2 ሜትር ከ10 ሴንቲ ሜትር የሆነ ርዝመት ነበረው፤ 130 ኪሎ ግራም ይመዝን ነበር። እርሱ በትክክል ለሥራው የተፈጠረ ሰው ነበር። ቦብ  በጆርጂያ ግዛት በሳቫና ከተማ የሚገኝ የእስረኞች ማቆያ ማዕከል የጸሎት አስተባባሪ ነበር። በየሳምንቱ ቦብ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶችን ይመራ፣ ጸሎት ያካሂድ እና ነፍሰ ገዳዮችን፣ ሌቦችን፣ ሴት ደፋሪዎችን እና ሁሉንም ዓይነት ወንጀለኞችን ያገለግል ነበር።

እነዚህን አገልግሎቶች በመደበኛ ሁኔታ የሚከታተል አንድ ሰው ነበረ። ይህ ሰው እምነቱን በክርስቶስ ላይ ለማድረግ ፈቃደኛ አልነበረም። እና መጥቶ ከርቀት ሲመለከት ቆይቶ የራሱን ጉዳይ ለመፈጸም ትቶ የሚሄድ አንድ ሰው ነበር።

ከጥቂት ወራት በኋላ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ላይ ያ ሰው እጁን አንስቶ በኢየሱስ ማመኑን እና አዳኙ መሆኑን መሰከረ። ሰው ሁሉ ተገረመ! ይበልጥ በማወቅ ፍላጎት ተይዞ ቦብ፥ "ለምን ክርስቲያን ሆንክ?" ብሎ ጠየቀው። ሰውየውም "ክርስቲያን የሆንኩት አንተ የራስህን ቢሮ እራስህ ስታጸዳ ስላየሁህ ነው።" ብሎ መለሰ። ልትገምቱ እንደምትችሉት የእስረኛው መልስ የበለጡ ጥየቄዎችን የሚያስነሳ ነው።

ከዚያም ሥልጣን ያላቸው ሰዎች ሁልጊዜ ከስራቸው ያሉ ሰዎች ላይ በመጫን የራሳቸውን ነገር ብቻ እንደሚያመቻቹ አብራራ። ስለዚህም እርሱ ለክርስቶስ አገዛዝ እራሱን ቢሰጥ ኢየሱስም ተመሳሳዩን እንዳያደርግበት ሰግቶ እንደነበር እና ያ ፍርሃቱ ግን ቦብ ቢሮውን እራሱ ሲያጸዳ ሲያይ እንደለቀቀው ገለጸ። በርካታ የእስር ቤት አጋሮቹ (የሱ ቢጤ ታሳሪዎች) የቦብን ቢሮ ለማጽዳት ጠይቀውት እንደነበር አስተውሏል። ነገር ግን ቦብ እነርሱን መጠቀሚያ ከማድረግ በትሕትና ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል።

እስረኛው ነገሮቹን እንዲህ ነበር ያያያዛቸው። ቦብ እንደ ክርስቶስ ተከታይ በሥሩ ባሉ ሰዎች ተጠቃሚ ካልሆነ፥ ኢየሱስም እንደዚያው የሚሆንበት ዕድል አለ ማለት ነው። እንደ ወለል ማጽዳት ያሉ በጣም ቀላል ተግባራት የእግዚአብሔር ሰውን መልካም ባሕርይ ለማሳየት እና ለማሳመን እግዚአብሔር ይጠቀምባቸዋል።

ኢየሱስ ሰዎች "መልካሙን ሥራችሁን አይተው አባታችሁን እንዲያከብሩ" ባለው መልኩ እንድንኖር ተናግሯል። የሰዎችን አትኩሮት ወደ ራሳችን ለመሳብ ብለን መልካም ሥራ ወደ ማድረግ ልንገባ አይገባም። የእኛ ተግባራት ለአባታችን እግዚአብሔር ክብርን ለማሰጠት የታሰቡ ናቸው።

በዚህ ምንባብ ውስጥ የሚገኘው መርህ ክርስቲያኖች ስለምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ በደንብ የምናስብባቸው እንድንሆን ሊያበረታታን ይገባል። የምንኖርበት አኗኗር አብዛኛውን ጊዜ ከምንናገረው የበለጠ ኃያል ነው።

- ሌሎችን ማገልገል ከፍቅር ልብ ሊመነጭ ይገባዋል። ሌሎችን ለማገልገል ተጨማሪ በሮች እንዲከፈቱላችሁ ልታደርጓቸው የምትችሏቸው ማስተካከያዎች አሉን?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

- አሁን ባላችሁበት ወቅታዊ ዐውድ ውስጥ ለክርስቶስ እንዴት የበለጠ ደምቃችሁ ልትበሩ ትችላላችሁ?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ለሌሎች ያለን አያያዝ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ የሚስብ ነው፤ ወይም ከክርስቶስ የሚያርቅ ነው።

**የጸሎት ጥቆማ፤** “ጌታ ኢየሱስ ላውቅህ እሻለሁ። ሌሎችም እንዲያውቁህ እፈልጋለሁ። እንቅስቃሴዎቼ በዙሪያዬ ባሉ ሰዎች ሲታዩ እንዴት እንደሚታዩ ለማሰብ እንድችል እርዳኝ። ሕይወቴ ክብርህን የሚያንጸባርቅ ይሁን! በኢየሱስ ስም ጸለይኩ። አሜን!”

**ለተጨማሪ ጥናት የሚሆኑ ምንባባት፤** ማቴዎስ 5፥13-16፣ የሐዋርያት ሥራ 4፥32-35፣ ፩ኛ ተሰሎንቄ 2፥1-12፣ ቲቶ 3፥14።

ማስታወሻ፤

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

## 2ኛ ቀን፥ ዕቅድ አንድ ላይ ሲመጣ (ሲያያዝ)

*“እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን።”* (ኤፌሶን 2፡10)

ሁላችንም የምንወዳቸው የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ይኖራሉ። በአስራ ዘጠኝ ሰማኒያዎቹ ይተላለፉ ከነበሩት ብዙ መልካም ዝግጅቶች ውስጥ የኛ ቤተሰብ ከአምልኮ በሚቀራረብ መሰጠት ከሚያዩዋቸው ፕሮግራሞች አንዱ ኤ-ቲም የሚሰኘው ነበር። ስርጭቱ ስሜት ቀስቃሽ ነበር ሙዚቃው ተደልቆ ይጀመራል። ሴራው ከሳምንት ሳምንት ፍጹም ተመሳሳይ ነበር። አስቀድማችሁ ሦስት ተከታታይ ክፍሎችን ካያችሁ በሚቀጥለው ሳምንት የሚተላለፈው ምን እንደሚሆን 80 ፐርሰንት ያህሉን እርግጠኛ ሆናችሁ መገመት ትችላላችሁ። ጭብጡ ሁልጊዜ አንድ ዓይነት ነበር።

አንድ ሰው በችግር ይገባል። ከዚያም ኤ-ቲም ችግሩን እንዲፈታ ይቀጠራል። ሃኒባል (የቡድኑ አባል) ሁሌ የመፍትሔ ዕቅድ አለው። መርዶክ ደግሞ እንደ እብድ እየተሯሯጠ የሚያደርገውን ያደርጋል። “ፌስማን” ሁሉንም ሴቶች ከአደጋው ያርቃል፤ ቢ ኤ ደግሞ በሦስት የቧንቧ ቁራጮች፣ በቧንቧ ማያያዣ ጥቅል፣ እና ትናንሽ ሚስማሮች በመጠቀም አስራ አራት መሣሪያዎች ይሠራል። በእቅዳቸው መሠረት የሚያመልጡትና ከችግሩ የሚወጡት በጣም በመከራ ነው። ከዚያም ሁሉም ከወጡ በኋላ ሃኒባል ዘና ብሎ ይቀመጥና፥ “እቅድ አንድ ላይ ሲሰምር ደስ ይለኛል።” ይላል። እንዴት ያለ ድንቅ ትእይንት! ስለነዚህ ተከታታይ ትዕይንቶች ተመልሼ ሳስብ፤ ለአንዷት ጊዜም ቢሆን የሃኒባል “እቅድ” ያልሠራበትን ክፍል ማስታወስ አልችልም። እርሱ በቲቪ ላይ ያለ በጣም አስደናቂ አዋቂ ወይም ዕድለኛው ሰው ነው። በሁለቱም መንገድ ይሁን ትዕይንቱ አዝናኝ ነበር።

ኤፌሶን 2፡10 ላይ እቅድ ያለው ሃኒባል ብቻ እንዳልሆነ እናያለን። በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት እግዚአብሔር በእኛ ሕይወት ሌሎችን በመርዳት እንድናሳልፍ አቅዷል። ከዘለዓለም በፊት ጀምሮ እግዚአብሔር የወደፊቱን አይቶ ችግሮችን ተረድቷቸዋል፤ ብሎም በጥበብ እነዚህ ችግሮች የሚፈቱበትን ዕቅድ ነድፏል። ያ የእግዚአብሔር ዕቅድም የእርሱ በሕዝቦቹ አማካኝነት ተገልጦ መኖር እና የእርሱ ሕዝቦችም ሕይወታቸውን ሌሎችን በመርዳት እንዲያሳልፉ ነው።

እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች መሻታችን በመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ማደግ ብቻ ሳይሆን መሻታችን በዓለም ዙሪያ ባለው የእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ መሳተፍም መሆን አለበት። ዓለምን ማገልገል መልካም ነገር ብቻ አይደለም፤ የእግዚአብሔር እቅድም ነው። እኔና እናንተ እርስ በእርሳችን እና ዓለምን ስናገለግል የሕይወታችንን ትክክለኛ ንድፍ እየኖርን ነው ማለት ነው።

ሌሎችን ለማገልገል እግዚአብሔር እንዴት ሊጠቀምባችሁ ይችላል? ስጦታችሁ የሆኑ አቅጣጫዎችን እና እናንተ ጥልቅ ፍላጎት ያላችሁን አቅጣጫዎች አስቡ።

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

እግዚአብሔር ለአገልግሎት ከፈጠረን እና ሕይወታችንን ሌሎችን ለማገልገል እንድንሰጥ ካቀደ ላለማገልገል ብንመርጥ ምን ይሆናል?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**የጸሎት ጥቆማ፤** “ጌታ ኢየሱስ ላውቅህ እሻለሁ። አንተ ለሕይወቴ እቅድ እንዳለህ እና ያም ዕቅድ ሌሎችን ማገልገል እንደሆነ አይቻለሁ። የአገልግሎት ዕድሎችን ለማየት እንድችል ትረዳኛለህን? እንዲሁም ጊዜው ሲመጣ ለማገልገል ድፍረትን ስጠኝ። ጌታ እወድሃለሁ! በኢየሱ ስም ጸለይኩ። አሜን!”

**ለተጨማሪ ጥናት የሚሆኑ ምንባባት፤** ዘፍጥረት ፩፥26-31፣ እና ፪፥4-8፣ ፩ኛ ጴጥሮስ ፪፥9-12።

ማስታወሻ፤

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

## 3ኛ ቀን፥ የምንከተላቸውን መምሰል

*“በእናንተስ እንዲህ አይደለም፤ ነገር ግን ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን፥ ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የእናንተ ባሪያ ይሁን፤ እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።”* ማቴ. 20፥26-28

አንድን ሰው ጣዖት አድርጋችሁ ታውቃላችሁን? አንድን ሰው ስለማምለክ ወይም አምላክ ናቸው ብሎ ስለማሰብ አይደለም የምናገረው። የምናገረው በጣም በጣም በጣም እነዚያን ሰዎች መምሰልን ስለመፈለግ ነው። ብዙ ሰዎች ወደ ቀድሞ የሕይወት ዘመናቸው መለስ ብለው ሲያዩ የሚያስታውሱት ኳስ ተጫዋች፣ ተዋናይ፣ ሙዚቀኛ ወይም በትምህርት ቤት ያለ ሁሉን የተቆጣጠረ የሚመስል ልጅ ነው የሚያስታውሱት። እንደነዚህ ዓይነት ሰዎችን ለመምሰል የማናደርገው ነገር አልነበረም።

ሌሎችን ጣዖት ከማድረጋችን የተነሣ የምናደንቃቸውን ሰዎች መኮረጅ ይቀልለናል። ግዙፍ የገበያ ተቋማት በዚህ ክስተት ለዓመታት ተጠቃሚ ሆነዋል። ጫማ፣ መነጽር፣ ሰዓት ወይም አልባሳትን በፈጣን ለመሸጥ የሚያስችለው ዘዴ ታዋቂ ሰው በሕዝብ ፊት አድርጎት እንዲታይ ማድረግ ነው። የፋሽን ምርጫችንን ሌሎችን በማድነቅ ላይ ተመስርተን መወሰናችን ጎጂ ያልሆነ ቢመስልም ለመኮረጅ ያለን ፍላጎት በፋሽን ብቻ የሚያበቃ አይደለም። እንደ መጠጥ፣ የፍቅር ግንኙነት፣ ዝንባሌ፣ ያለቅጥ የበዛ እዳ፣ እና ሌሎችን የምንይዝበት ልማድ ሳይቀር ያሉ የሕይወት ውሳኔዎች ወደ ኋላ ቢፈተሹ የምናደንቀውን ሰው ከመኮረጅ/ከመምሰል ጋር የተያያዙ ሆነው ሊገኙ ይችላሉ።

ነገር ግን መኮረጅ ሁል ጊዜ መጥፎ ነገር አይደለም። በእርግጥ ለመምሰል ያለን መሻት በእግዚአብሔር በራሱ እኛ ውስጥ የተቀመጠ ነው። መምሰላችን የእግዚአብሔርም መሻት ነው፤ ይህ ታዲያ ከዓለም አቅጣጫ ጋር ሳይሆን ነገር ግን ከእግዚአብሔር ባህርይ ጋር ነው፤ (ሮሜ 12፡2)።

የሚያሳስተው ክፍል ይሄ ነው! ሰዎችን እንዲኮርጁ ወይም እንዲመስሉ ማድረግ ከባድ አይደለም። ጉዳዩ ሰዎችን ክርስቶስ የዓይናቸው አምሮት ሊሆን እንደሚገባው ማየት እንዲችሉ መርዳት ነው። ክርስቶስ እጅግ የምናደንቀው፣ እጅግ የምናከብረው፣ ከሁሉ በላይ የምንወደው እና ከሁሉ በላይ ዋጋ የምንሰጠው ብቸኛው ሲሆን ልንመስለው የምንፈልገው ብቸኛው እርሱ ይሆናል።

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ሌሎችን እንዲረዱ አስተምሯቸዋል። እያንዳንዱ አማኝ ከክርስቶስ ጋር ባላቸው ግንኙነት ሲያድጉ ለማገልገል ታላቅ መሻት ይኖራቸዋል። እግዚአብሔርን በፍቅር ግንኙነት ስንከተለው መንፈስ ቅዱስ ባህርያችን ክርስቶስን እንዲመስል ይለውጠዋል። ግባችን እርሱን መውደድ ነው፤ ነገር ግን በሂደት የምንከተለውን እርሱን እንመስላለን።

- በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልግላችሁ ሙሉ ስሜት የማይሰጥ ሆኖ አግኝታችሁ ታውቃላችሁን? የት ነው ያገለገላችሁት? እናም ለምንድን ነበር እዚያ ለማገልገል የመረጣችሁት?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

- ከላይ በሰጣችሁት መልስ ላይ ተመርኩዛችሁ እግዚአብሔርን መውደድ ላይ ብታተኩሩ እና አገልግሎታችሁን ከዚያ ፍሰጋ የሚመነጭ እንዲሆን ብታደርጉ የቀደመ ልምምዳችሁ የተለየ ሊሆን እንደሚችል ታስባላችሁን?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

- በየዕለቱ እንዴት እንደምትኖሩ ባለው ሁኔታ ላይ በመመሥረት ኢየሱስ የዓይናችሁ አምሮት እንደሆነ ይመስላችኋልን? ወይስ ሌሎችን ጣዖት ስታደርጉ እራሳችሁን ታገኛላችሁን? ከሆነ ማንን ነው ጣዖት የምታደርጉት? እና ለምን?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**የጸሎት ጥቆማ፤** “ጌታ ኢየሱስ ላውቅህ እና አንተን ልመስል እሻለሁ። ሌሎችን እንዳከብር፥ ነገር ግን አንተን ብቻ እንድመስል እርዳኝ። በኢየሱስ ስም ጸለይኩ። አሜን!”

**ለተጨማሪ ጥናት የሚሆኑ ምንባባት፤** ሉቃስ 22፥24-27፣ ፊልጵስዩስ 2፥1-11።

# 4ኛ ቀን፥ በትዕቢት ላይ እርምጃ መውሰድ

*“እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፥ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል ይላል። . . . በጌታ ፊት ራሳችሁን አዋርዱ ከፍ ከፍም ያደርጋችኋል።” ያዕቆብ* 4፡6 እና 10

እኔ ትዕቢት አይገባኝም። ነገሩን ለማብራራ ብቃት ስለሚጎድለኝ ሳይሆን ሰዎችን የሚስብበትን ነገር ለማብራራት አዳጋች ሆኖ ስለማገኘው ነው። ትዕቢትን ለማስወገድ ለምን ከባድ ነገር ሆነ?

እንደ ትዕቢት ተመጣጣኝ ተግሳጽ እና ቅጣት የሚቀበል ሌላ ኃጢአት በፍጹም የለም። ሆኖም እንደ ትዕቢት በአማኞች ሕይወት እጅግ የተለመደ ሌላ ኃጢሕት የለም። ትዕቢት ወደ የመጀመሪያው ኃጢአት ወደ ሰይጣን ውድቀት፣ ወደ ባቢሎን የቋንቋ መከፋፈል፣ ወደ ናቡከደነፆር ውርደት፣ ወደ የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የክርስቶስ መገፋት እና በነገሮች ሁሉ በእግዚአብሔር መደገፍን እንቢ ወዳልንበት የኃጢአት ሥር ተወርዶ ቢፈለግ ሊገኝ የሚችል ነው። በኃጢአት ስር ውስጥ የትዕቢት ነገር አለ።

የትዕቢት ኃጢአትን እንዴት በተግባር ምላሽ ልንሰጠው እንችላለን?

ለዚህ ጥያቄ ምርጡ መልስ የክርስቶስን ምሳሌ መከተል ነው። ኢየሱስ ግንኙነቱን ከአብ ጋር እንዲሆን አጥብቆ ይከታተል ነበር። እናም እራሱን የሌሎች አገልጋይ አድርጎ ነበር። (ሮሜ 15፥8) ግንኙነቱ በአብ ላይ ጥገኛ ሆኖ እንዲቀጥል አደረገው፤ እናም የአገልግሎት አቋሙ የትሕትና መስመሩን እንደጠበቀ እንዲኖር አደረገው። ክርስቶስ ምንም እንኳን “እንደ እኛ በነገር ሁሉ የተፈተነ ቢሆንም” ያለኃጢአት ነበር የዘለቀው። (ዕብራውያን 2፥17-18፣ 4፥15፣ ማቴዎስ 4) ክርስቶስ ግንኙነትን አጥብቆ ተከታተለ እናም እራሱን በአገልግሎት ጎዳና ላይ አስቀመጠ።

ከትዕቢት ጋር ስንታገል ዕቅዳችን ተመሳሳይ ሊሆን ይገባል። ጌታን በፍቅር ግንኙነት በመከተል እንጀምር። ስትከተሉት እግዚአብሔር የአገልግሎት ስፍራዎችን እንዲገልጥላችሁ ጠይቁት። እግዚአብሔርን በመከተል እና በትሕትና ሌሎችን በማገልገል በንቃት እና ገና ሳይመጣ ከትዕቢት ጋር ያለብንን የግል ትግል እንጋፈጣለን።

- ስለማገልገል ያሉባችሁ ፍርሃቶች ምን ምን ናቸው?

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------

- ብዙ ሰዎች የእውቅና፣ የአድናቆት፣ እና የተቀባይነት ማግኘት ፍላጎት አላቸው። አብዛኛዎቹ የአገልግሎት መደቦች ደግሞ እነዚህን ነገሮች አያሰጡም። ይህንን ጉዳይ እግዚአብሔር እንዴት ነው በማቴዎስ 6፥1-4 እና በማቴዎስ 25፥31-40 መሠረት ምላሽ የሚሰጠው?

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------

- ከዚህ በፊት የትዕቢትን ኃጢአት እንዴት ነው ምላሽ ልትሰጡ የሞከራችሁት? ምን ያህል ሠራላችሁ?

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ከማገልገል የሚያስቀረን ኃጢአት ትዕቢት ነው። የትዕቢት መከላከያው ደግሞ የትሕትና አገልግሎት ነው። የአገልጋይን የሥራ መደብ ከያዛችሁ ሌሎችን ወደታች ለመመልከት አዳጋች ነው።

**የጸሎት ጥቆማ፤** "ጌታ ኢየሱስ ላውቅህ እና የሄድክበትን መንገድ ልከተል እፈልጋለሁ። በቃሉ መርህ መሠረት እራሴን ትሑት ማድረግ እንዳለብኝ አውቃለሁ። ይህንን ኃላፊነት የምሬን ወስደዋለሁ። በራሴ መንገድ ለማድረግ ስለነበረኝ መሻት በመናዘዝ መጀመር እፈልጋለሁ። አንተን ስከተል አንተም ትዕቢቴን እንድታስወግድልኝ እጸልያለሁ። የአገልግሎት ስፍራዎችን እንድፈልግ እርዳኝ። በኢየሱስ ስም ጸለይኩ። አሜን!"

**ለተጨማሪ ጥናት የሚሆኑ ምንባባት፤** ሮሜ 12፥3-8፣ ገላትያ 6፥1-4።

ማስታወሻ፤

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------

## 5ኛ ቀን፥ እንደዚህ ጊዜ ሙሉነት (እርካታ) ተሰምቶኝ አያውቅም

ምላሹ የተለመደ ነው። አማኝ ሌሎችን ለማገልገል ድፍረቱን እየገነባ ይሄዳል። ካጠናቀቁ በኋላም "በጣም ደስ ብሎኛል፤ በእርግጥ በሕይወቴ እንደዚህ ሙሉነት እና እርካታ ተሰምቶኝ አያውቅም።" ይላል።

ክርስቲያኖች የሚዘነጉት አንድ ነገር ይህ ስሜት ለምን እንደሚሰማቸው ነው። በአጭሩ የተሠራንበት ዲዛይን እርካታን ወይም ሙሉነትን ይወስናል። ለደቂቃ የተቀደሰ እይታችሁን መለስ ብላችሁ እዩት፤ ደግሞም እነዚህን ጥያቄዎች በመጠየቁ እንደ እብድ አትቁጠሩኝ። አውሮፕላን ስሜት ቢኖረው እርካታ የሚሰማው በመሬት ሲሆን ነው ወይስ በዳመናት መሃከል ሲበር? የውድድር መኪና እንዲሁ ማሰቢያ ኖሮት ተመሳሳይ አሳቦችን ቢያሳይ በማቆሚያ ስፍራ ሆኖ ነው? ወይስ በውድድር መሃል የበለጠ እርካታ የሚሰማው? ጀልባ ማውራት ቢችል የበለጠ እርካታ የሚሰማው በደረቅ ዳርቻ ላይ ሲቆም ነው ወይስ በማዕበል መሃል ባህሩን እየሰነጠቀ ሲሄድ ነው?

ሕያው ያልሆኑ ቁሶችን (እንደ አውሮፕላን፣ የውድድር መኪና ወይም ጀልባ ያሉ) ቅርጽና አሠራር መመልከት እና ዓላማውን እያሳካ መሆኑን ማወቅ ለኛ ቀላል ነው። ዲዛይን ወይም የተበጀንበት ማንነት የስኬት መጠንን ይወስናል። በሆነ ምክንያት ተመሳሳይ መርሕን በሰዎች ላይ መጠቀም አስቸጋሪ ይሆንብናል። በሰውነታችን በጋራ ባለን ዲዛይን ላይ ከማተኮር ይልቅ የራሳችን የግል ዲዛይን ላይ የበለጠ እናተኩራለን።

ሰዓሊያን ስሜታቸውን በቅብ ስዕል ሲገልጹ እርካታ እንደሚሰማቸው እናውቃለን። ተወዛዋዦች በእንቅስቃሴያቸው ስሜታቸውን ሲገልጹ እርካታ ይሰማቸዋል። የፈጠራ ሰዎች አዳዲስ አሳቦችን ሲያስቡ እርካታ ይሰማቸዋል። ሆኖም በእነዚህ ሁሉ አቅጣጫዎች ውስጥ ትኩረቱ በግል ዲዛይን (የተበጀንበት ማንነት) ላይ ያተኮረ ነው። እንደ ሰዎች ስላለን የተበጀንበት ማንነትስ? እግዚአብሔር ሰዎችን ተመሳሳይ የሙሉነት ስሜት (እርካታ) እንድንለማመድ ያበጀበት የሆነ ዲዛይን ይኖረው ይሆንን?

መልሱ "አዎ!" ነው። እግዚአብሔር ከራሱ ጋር ግንኙነት እንዲኖረን ነው የፈጠረን። ከዚያም ሌሎችን እንድናገለግል አደራ ሰጠን።

- "እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን።" (ኤፌሶን 2፥10)
- "በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ፥ ከማኅፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ፥ ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ።" (ኤርምያስ 1፥5)

- “ያዳነን በቅዱስም አጠራር የጠራን እግዚአብሔር ነውና፥ ይህም እንደ ራሱ አሳብና ጸጋ መጠን ነው እንጂ እንደ ሥራችን መጠን አይደለም፤ ይህም ጸጋ ከዘላለም ዘመናት በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ ተሰጠን፥” (2ኛ ጢሞቴዎስ ፤፥9)

ሰዎች ሌሎችን በማገልገል ሙሉነት እና እርካታ ሲሰማቸው ፈጽሞ ሊያስደንቀን አይገባም። ሙሉነት/እርካታ እንደተበጀነው/እንደዲዛይናችን የመኖር ተረፈ-ምርት ነው።

- በሕይወታችሁ እርካታን ለማግኘት ትግል ታደርጋላችሁን? ከሆነ ልታገለግሉባቸው የምትችሉባቸው አቅጣጫዎች ምን ምን ናቸው?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

- የተበጀንበት ማንነት (የተሠራንለት ዕቅድ) የኛን መሳካት/እርካታ የሚወስን ከሆነ ከዲዛይኑ ውጪ ሆኖ መኖር ወደ እርካታ እጦት ይመራል። በሕይወታችሁ ከእግዚአብሔር ዲዛይን ውጪ የኖራችሁባቸውን አቅጣጫዎችን ለይታችሁ ልታወጡ ትችላላችሁን?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**የጸሎት ጥቆማ**፤ “ጌታ ኢየሱስ ላውቅህ እሻለሁ! በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሕይወቴን ለግንኙነት እና ለአገልግሎት እንደፈጠርካት እና እንዳቀድካት አይቻለሁ። እርካታን ሳጣ ወደ ተበጀሁበት ዕቅድ እንድመለስ ማስታወስ እንድችል እርዳኝ። እወድሃለሁ። በኢየሱስ ስም ጸለይኩ፤ አሜን!”

ማስታወሻ፡

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

# 6ኛ ቀን፥ ክርስቶስን ለማካፈል ምቹ ዐውድ መፍጠር

*"በጸሎታችን ጊዜ ስለ እናንተ ስናሳስብ፥ የእምነታችሁን ስራ የፍቅራችሁንም ድካም በጌታችንም በኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን የተስፋችሁን መጽናት በአምላካችንና በአባታችን ፊት ሳናቋርጥ እያሰብን፥ እግዚአብሔርን ሁል ጊዜ በሁላችሁ ምክንያት እናመሰግናለን፤ ... ከእናንተ ወጥቶ የጌታ ቃል በመቄዶንያና በአካይያ ብቻ አልተሰማምና፥ ነገር ግን ምንም እንድንናገር እስከማያስፈልግ ድረስ፥ በእግዚአብሔር ዘንድ የሚሆን እምነታችሁ በሁሉ ስፍራ ተወርቶአል።"* 1ተሰ. 1፥2-3 እና 8።

ክርስቶስን ማካፈል ዕድል ነው ወይንስ መብት? በአሜሪካ ለሰዎች መብቶቻችንን ለመንገር ፈጣን ነን። በነጻነት የመናገር መብት አለን። በጋራ ለአምልኮ የመሰባሰብ መብት አለን። ለተቃውሞ በሰላማዊ መንገድ የመሰባሰብ መብት አለን። መብቶቻችን የላቀ ጥበቃና እንክብካቤ የሚደረግላቸው ናቸው። እኔ እየተደሰትንባቸው ስላሉ መብቶች ፍጹም ባለ ውለታ መሆኔ እንዳለ ሆኖ ቤተ ክርስቲያን መብቶችን ከመልካም ዕድሎ ጋር እያሳሳተች እንዳይሆን እፈራለሁ።

በቅርብ በተሰበሰበ የሕዝብ አስተያየት አሜሪካውያን "ክርስቲያን" የሚለውን ቃል ሲሰሙ በመጀመሪያ የሚሰማቸውን ስሜት እንዲናገሩ ተጠይቀው ነበር። የመጀመሪያዎቹ ብዙ ቁጥር ያገኙ ሦስት ምላሾች ፈራጅ፣ ኩናኝ እና ግብዝ የሚሉ ነበሩ። ይህ ፍጹም ግልብ መልስ አልነበረም! አሜሪካውያን ክርስቲያኖች መብታችን በመሆኑ ተነስተን ከምንናገረው እንጂ ከተግባራችን አይተው ነው እውነታውን ያስቀመጡት። እኛ ለኢ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አቋሞች ስንል ከንግድ አሻፈረኝ ብለን እንወጣለን። የውርጃ ክሊኒኮችን ሕይወት የሚያጠፉ ስለሆኑ እንቃወማለን። የግብረ ሰዶማውያን መብትን ተቃውመን እንሰለፋለን። ስለ ደረቅ ወረዳዎች ተፈራርመን ለኮንግረስ እናቀርባለን፤ ብሎም ጸሎት ወደ ትምህርት ቤቶች እንዲመለስ እንጠይቃለን። ነገር ግን ሁል ጊዜ ነገሩን የሚያስደርገን መነሳሻችን "የመናገር ነጻነት አለን፤ የመቃወም ነጻነት አለን እና አመለካከታችንን ለማካፈል ነጻነት አለን።" የሚለው አሳብ ነው። ከሕግ አንጻር ለመቃወም መብት አለን፤ በተግባር ግን መልካም ዕድሉን አጥተን ሊሆን ይችላል።

ክርስቶስን ማካፈል ዕድል ነው። በቃሉ ውስጥ ኢየሱስ እንዲሰሙት ሲያስገድድ የሚያሳይ አንድም ስፍራ የለም። ይህ አላስፈለገውም ነበር። ይልቁንም ኢየሱስ የተጎዳውን ፈውሶ ከዚያም መልእክቱን አካፍሏቸዋል። ረዳት አልባውን ነክቶ ከዚያ ስለ መንግሥቱ አስተምሯቸዋል። የክርስቶስ የአገልግሎት ተግባር ለውይይት በር ይከፍት ነበር።

በተሰሎንቄ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን የሚታወቁ የነበሩት "ስለ እምነት ሥራቸው፣ ስለ ፍቅር ትጋታቸው እና ስለ ተስፋ ጽናታቸው" ነበር። ለሌሎች ሲያገለግሉ፣ እምነታቸውን በሥራ ሲገልጹት እና በትጋት ፍቅርን ለሚያምኑትም ሆነ ለማያምኑት በተመሳሳይ ሲያሳዩ "የጌታ ቃል . . . በሁሉ ስፍራ ተወርቶአል።" የእግዚአብሔር ቃል ከእነርሱ የአገልግሎት ተግባር የተነሣ አበበ።

ባለፉት አምስት ቀናት ዓለምን ማገልገል ለአብ ክብርን ማምጣቱን፣ የእግዚአብሔር ዕቅድ አካል መሆኑን፣ ከክርስቶስ ባህርይ ጋር እንደሚያመሳስለን፣ ከትዕቢት በተቃራኒ እንደሚያቆመን፣ እና ለሕይወታችን ሙሉነትን/እርካታን እንደሚያመጣ አይተናል። ዓለምን ማገልገል የሚለውን ጥናታችንን ስንጨርስ አገልግሎታችን ክርስቶስን ለማካፈል ምቹ ዐውድ እንደሚፈጥርልን ልንመለከት ይገባል። ሌሎችን ስናገለግል እግዚአብሔር የምሥራቹን ቃል የምናካፍልበትን ዕድል ይፈጥርልናል።

ይህን የጥሞና ትምህርት ስታጠናቅቁ የአኔን የልብ አሳብ አሳስታችሁ እንደማትረዱ ተስፋ አለኝ። ቤተ ክርስቲያን መብቶቿን ማጣት አለባት ብዬ እየጠቆምኩ አይደለም፤ እኔ እየጠቆምኩ ያለሁት መናገር ያለብን በአገልግሎታችን ነው የሚለውን ብቻ ነው። በአሜሪካ ያለችው ቤተ ክርስቲያን በምንወደው ክርስቶስ እንጂ በምንጠላቸው ጉዳዮች የምትታወቅ እንዳትሆን ጸሎቴ ነው።

- እራሳችሁን የምታገኙት ለመሰማት ስትጠይቁ ነው ወይስ እንድትናገሩ ስትጠየቁ ነው? ለምን?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

- ኢየሱስ በመጀመሪያ አገልግሎ ከዚያም ትምህርቱን ያካፈለበት ቅደም ተከተልን የሚያሳዩ ልዩ ልዩ ታሪኮች ዘርዝሩ።

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**የጸሎት ጥቆማ፤** “ጌታ ኢየሱስ ላውቅህ እሻለሁ። ወንጌልህንም ለሌሎች ላካፍልም እፈልጋለሁ። አንተ የኖርክበትን አኗኗር ቅደም ተከተል ተግባራዊ እንዳደርግ እርዳኝ። አሜን!”

ማስታወሻ፤

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------



# ሳምንት አራት

# ወንጌሉን አደራ ስጡ።

## 1ኛ ቀን፥ አደራ መስጠት ማለት ምን ማለት ነው?

*"እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።"* ማቴዎስ 28፥19-20

*"ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ።"* 2ኛ ጢሞቴዎስ 2፥2

በዚህ ሳምንት ወንጌሉን አደራ በመስጠት ላይ እናተኩራለን። በዚህ መምሪያ ላይ ከቀረቡት የአራት ሳምንት ትምህርቶች መካከል ወንጌሉን አደራ መስጠት ምናልባት ከሁሉ ከባዱ አሳብ ሳይሆን አይቀርም። ግልጽ ለማድረግ ሲባል የመጀመሪያዎቹን ሁለት ቀናት አጠቃላይ ምስሉን በማሳየት ላይ እንቆያለን።

ከላይ በቀረቡት ምንባባት (ማቴ. 28 እና 2ጢሞ. 2) በሁለቱም ውስጥ የተቀበልነውን ለሌሎች የማስተላለፍ ሞጋች ፈተና ቀርቦልናል። ኢየሱስ ተከታዮቹን "ያዘዝኋችሁን ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው" ብሎ ደቀ መዛሙርት እንዲያደርጉ ነግሯቸዋል። እነርሱም የተማሩትን እንዲስተላልፉ ተነግሯቸው ነበር። በጢሞቴዎስም ተመሳሳይ ነበር የሆነው። ጢሞቴዎስ ጳውሎስ ለእርሡ ያካፈለውን ነገር ለሌሎች እንዲያስተላልፍ ፈተና ቀርቦለት ነበር። በእነዚህ ሁለት ምንባባት ውስጥ የተላለፈው ነገር ምንም ይሁን በሌሎች ላይ ተጽእኖ መፍጠሩን ይቀጥላል፣ ለራሳችን የጠበቅነው ወይም በእኛ ውስጥ ያስቀመጥነው ምንም ነገር እኛ ስንሞት አብሮን ይሞታል።

ሁላችንም ስንሞት ምንም ነገር ከእኛ ጋር ይዘን እንደማንሄድ እያወቅን ነው የምንኖረው። ወደዚህ ዓለም የመጣነው ምንም ሳንይዝ ነው እናም ልክ እንደመጣንበት ሁኔታ ስንሄድም በተመሳሳይ መልኩ ነው። ስለዚህ ለራሳችን የያዝነው ምንም ነገር (ለምሳሌ፣ አሳቦች፣ እውቀት፣ ሃብት፣ እና ማበረታቻዎች ወዘተ፥) ስንሞት ይሞታል። ለወደፊትም ምንም ተጽእኖ አይኖረውም።

ስለ ተጽእኖ አስቡ እና እግዚአብሔር ያስተማራችሁን ትምህርቶች በሙሉ ከግምት አስገቡ። እርሱ ስለ ቃል ምን አስተምሯችኋል? ስለ እምነትስ ምን አስተምሯችኋል? ስለ ግንኙነት፥ ስለ ቤተሰብ፥ ስለ ጸሎት ምን አስተምሯችኋል? እግዚአብሔር በእኛ ላይ የሕይወት ዘመን እውነታዎችን ማፍሰሱ እና እኛም ያንን ሁሉ እውቀት ወደ መቃብር ይዘን መሄዳችን ትርጉም የሚሰጥ ነገር ነውን?

እግዚአብሔር ለእኛ ያስተላፈውን ነገር ለሌሎች እንድናስተላልፍ ይፈልጋል? አደራ የመስጠት የመጀመሪያው እርምጃ እግዚአብሔር የእኛ ሕይወት የእርሱ እውነታዎች እና ጸጋ ቱቦዎች እንዲሆኑ እንደሚፈልግ ማወቅ ነው።

- በሕይወታችሁ ላይ ጊዜያቸውን እና እውነትን ያፈሰሱ ሰዎችን ስም ዘርዝሩ። (ወደ ኋላ ተመልሳችሁ መጋቢያንን፣ የሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪዎች፣ የጥናት ቡድን መሪዎች፣ ሁለኛ የሕይወት ምሳሌዎች፤ ወይም ጥሩ ጓደኞች።) እነዚህ ሰዎች እውነትን በእናንተ ውስጥ በእምነት ባያኖሩ ዛሬ እናንተ በመንፈሳዊነት የት ትሆኑ ነበር?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሳል አማኝ እውነትን እና ጊዜውን ለሌላ(ሎች) ያስተላለፉበትን ግንኙነት ታውቃላችሁ? ከሆነ የተለያዩ ምሳሌዎችን ዘርዝሩ።

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**የጸሎት ጥቆማ፤** "ጌታ ኢየሱስ ላውቅህ እፈልጋለሁ። ሌሎችም እንዲያውቁህ እፈልጋሁ። በሕይወቴ ወደ ኋላ ተመልሼ ስመለከት ምን ያህል እንዳስተማርከኝ አስታውሳለሁ። እነዚህን እውነቶች ለሌሎች እንዴት ማስተላለፍ እንደምችል እንድረዳ ልትረዳኝ ትችላለህን? በኢየሱስ ስም ጸለይኩ፤ አሜን!"

**ለተጨማሪ ጥናት የሚሆኑ ምንባባት፤** ማቴዎስ 10፥1-16፤ የሐዋርያት ሥራ 1፥8፣ 2ኛ ቆሮንቶስ 5፥17-20።

ማስታወሻ፤

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

## 2ኛ ቀን፥ ወንጌሉን አደራ መስጠት

“ወንጌል” የሚለው ቃል “የምሥራች ዜና” ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ወንጌል ሲናገር የእግዚአብሔር የምሥራች ዜና ማለቱ ነው። ይሁንና የእግዚአብሔር የምሥራቹ ቃል ከደኅንነት ግብዣ (የዘላለም ሕይወት) ያለፈ ነው። አንድ ጊዜ ሰዎች ከዳኑ እና ከእግዚአብሔር ጋር ከታረቁ በኋላ እንዴት መኖር እንዳለባቸው ያለውን አሳብም ያካትታል።

ጌታ ኢየሱስ የምድር አገልግሎቱን በጀመረ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ “ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ በገሊላ ሁሉ ይዞር ነበር።” (ማቴዎስ 4፥23፣ 9፥35፣ 24፥14፣ ማርቆስ 1፥14) ይላል። ይህ ምንባብ ለመጀመሪያ ጊዜ “ወንጌል” የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሰበት ክፍል ነው። አሳቡ በቀጥታ የመንግሥቱን ወንጌል የሚያወሳ ነው። በእርግጥ የመንግሥቱ ወንጌል በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተለመደ አገላለጽ ነው። (ማቴዎስ 9፥35፣ 24፥14፣ ሉቃስ 16፥16) የእግዚአብሔር የምሥራቹ ቃል ከመንግስቱ የምሥራች ዜና ጋር የተገናኘ ነው።

ስለ መንግሥት ትንሽ እናውራ። መንግሥቱ ማለት እግዚአብሔር እንዲሆን በሚፈልገው ነገር ዙሪያ የእግዚአብሔር ሙሉ ፈቃድ የመሆኑ ደረጃ ነው። እግዚአብሔር የሁሉ ነገር ፈጣሪ ሆኖ ሳለ መንግሥቱን በሕዝቡ መካከል መመሥረትን መረጠ። የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ ሚሄድበት የእርሱ ሉአላዊ ተጽእኖም አብሮአቸው ይሄዳል። እግዚአብሔር በሕዝቡ በኩል ሲኖር የእርሱ ተጽእኖ እና መንግሥት ይሰፋል።

መንግስቱ የኢየሱስ ትምህርት እና ስልጠና ዋና ትኩረት ነው።

- ኢየሱስ የመንግሥቱን ወንጌል ሰበከ (ማቴዎስ 4፥23፣ 9፥35፣ 24፥14፣ ማርቆስ 1፥14)።
- የተራራው ስብከት የመንግሥቱ መተዳደሪያ ደንብ (ሕገ መንግስት) ተደርጎ ይወሰዳል (ማቴዎስ 5፥7)
- ኢየሱስ በማቴ. 13 ሰባት ምሳሌዎችን ተናግሯል። የእያንዳንዱ ትኩረትም መንግሥቱ ነበር።

ይሄ ሁሉ ስለ መንግሥቱ መናገር ለምን አስፈላጊ ሆነ? መልሱ፥ ምክንያቱም ወንጌሉ “ኢየሱስ ያድናል” ከማለት ያለፈ ነው። በክርስቶስ እና በመጥምቁ ዮሐንስ የተሰበከው ወንጌል “የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንስሃ ግቡ።” የሚል ነው። እነርሱ የመንግሥቱን ወንጌል ሰበኩ። የምስራቹ ቃል እግዚአብሔር የዕርቅ ግንኙነት መፍቀዱ እና ማቅረቡ ነው። ደግሞም ይህ አዲስ ግንኙነት የሚኖረው በእግዚአብሔር መንግሥት ዐውድ ውስጥ የሚኖር ነው።

አማኞች የወንጌሉን ወሰን ሲረዱ ያ ሁሉንም ነገር ይቀይራል። አትኩሮታችንንም ይቀይራል። ለጠፉት የምናደርገውን ጥሪም ይለውጣል። ቅድሚያ የምንሰጠውን ነገር ቅደም ተከተል

ይለውጣል። ከሰዎች ጋር ያለንን ተግባቦት ይለውጣል። ጸሎታችንን ይለውጣል። ለዓለም ያለንን እይታ ይለውጣል። የገንዘብ አወጣጣችንን ይለውጣል። የምንቀርጻቸውን ግቦች እና እንዴት እነዚህን ግቦቻችንን እንደምንከተል ያለንን አካሄድ ሳይቀር ይለውጣል። መንግሥቱ የክርስትና ሕይወት ዐውድን ይሰጣል።

ወንጌሉን አደራ መስጠት የመንግሥቱን ወንጌል አደራ መስጠት ነው።

እግዚአብሔር በሕይወታችሁ ውስጥ እውነትን በአደራ የሰጠባቸውን አቅጣጫዎች ዘርዝሩ። (ለምሳሌ፡ ትዳር፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ ጸሎት፣ እምነት፣ ገንዘብ፣ ልጆች፣ ወዘተ፤) እግዚአብሔር ለእናንተ ያካፈላችሁን እናንተ በአደራ ልትሰጡ የምትችሉት የት ነው?

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**የጸሎት ጥቆማ፤** “ጌታ ኢየሱስ ላውቅህ እፈልጋለሁ። በቃሉ መሠረት ስለ መንግሥቱ ጭምር እንዳውቅ የምትፈልግ ይመስለኛል። በወንጌሉ መልዕክት ወሰን ልክ ዓይኖቼን እንድትከፍት እጸልያለሁ። እናም የተማርኩትን ለሌሎች በአደራ ማስተላለፍ እንድችል እርዳኝ። ስለምትወደኝ አመሰግንሃለሁ። በኢየሱስ ስም ጸለይኩ፤ አሜን!”

**ለተጨማሪ ጥናት የሚሆኑ ምንባባት፤** ኢሳይያስ 9፥1-7፣ ኤርሚያስ 31፥31-34፣ ማቴዎስ 5-7፣ ገላትያ 2፥7 1ኛ ተሰሎንቄ 2፡4።

ማስታወሻ፡

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

## 3ኛ ቀን፥ የግንኙነት ጎዳናዎች

ወንጌሉን አደራ መስጠት ትልቅ ሥራ መስሎ ሊታይ ይችል ይሆናል። አእምሮአችን እንዴት እንደምናካፍል ከማሰብ ይልቅ ፈጥኖ ምን እንደምናካፍል የመሳሰሉት አሳቦች ላይ ይሄዳል። “ምን?” የሚለውን በትናንቱ ትምህርት ተመልክተናል! እኛ ስለ መንግሥቱ የምሥራቹን ቃል ነው የምንናገረው። “እንዴት” የሚለውን ዛሬ እናያለን። በግንኙነት መረቦቻችን አማካኝነት ስለ መንግሥቱ የምሥራቹን ቃል ነው ልንናገር ነው ያለነው።

ሁሉ ነገር በግንኙነት ጎዳናው ላይ ይሮጣል ይባላል። ወንጌሉን አደራ መስጠት ለዚህ ተግባራዊ እውነት ትክክለኛ ምሳሌ ነው። ወንጌሉን ሙሉ ለሙሉ እንግዳ ለሆነ ሰው የማካፈል ዕድል የምናገኝባቸው ጊዜያት እንዳሉ ሆነው ወንጌሉን በአደራ የመስጠቱ መደበኛ አካሄድ የእኛን የግንኙነት መረቦች ያካተተ ነው። እነዚህ መረቦች ወዳጆችን፣ ቤተሰብን፣ የሥራ ባልደረቦችን፣ ጎረቤቶችን እና በቋሚነት ወይም በመደበኛ ሁኔታ የምንገናኛቸውን ሰዎች ያቀፉ ናቸው። ከቀደሙ ግንኙነቶች የተነሣ እነዚህ መረቦች ወንጌሉን በአደራ ለማስተላለፍ ለም አፈር ናቸው።

ወንጌል በግንኙነት መረቦች ውስጥ የሚያብብባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ።

- **የመጀመሪያው መልእክቱ ከግንኙነት ጋር የተያያዘ ባህርይው ነው።** በመንግሥቱ ወንጌል ውስጥ ሦስት ቁልፍ ግንኙነቶች ይካተታሉ። እነዚህም፥ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት፣ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለን የኛ ግንኙነት እና ከዓለም ጋር ያለን ግንኙነት ናቸው።
- **ሁለተኛ፥ መልእክቱ ማካፈል ጊዜ ወሳጅ መሆኑ ነው።** አንዳንድ አሳቦች በብጣሽ ወረቀት ላይ ላይ ጽፈን በቀላሉ በበቂ ሁኔታ ልናብራራቸው የምንችላቸው ሲሆኑ ስለ መንግሥቱ ማካፈል ግን እንደዚህ አይደለም። የመንግሥቱን ወንጌል ማካፈል ጊዜ ይወስዳል። ግንኙነቶች በስፍራቸው ከሆኑ ውይይቱን ለመቀጠል በርካታ ዕድሎ ይፈጠራሉ።
- **ሦስተኛ፥ የመልእክቱ ውጤት የተለወጠ ሕይወት ነው።** እግዚአብሔር ሕይወታችሁን እንዴት እንደለወጠ ለአንድ ፍጹም ለማታውቁት ሰው መንገር አንድ ነገር ነው። ነገር ግን ጥሩ ግንኙነት ባለበት ስትናገሩ የምትናገሯቸው ሰዎች ሙሉ በሙሉ ሊያዩ የሚችሉት በፊታቸው የቆመ አንድ ሰውን ነው። በግንኙነት መረቦቻችን የተካተቱት ሰዎች በሕይወታችን የሆነውን የእግዚአብሔርን ቀጣይ መለወጥ ተመልክተዋል። ይህ ለውጥ ደግሞ ወንጌሉን ለማካፈል ምቹ ዐውድ ይሆናል።

አዲስ ኪዳንን ስናነብ የመንግሥቱ ወንጌል በግንኙነቶች ውስጥ በአደራ ሲሰጥ እንመለከታለን። እግዚአብሔርም ተመሳሳይ ሁኔታ ይህ ቅደም ተከተል በሕይወታችን እንዲከናወን ይሻል። እያንዳንዱን ምንባብ ተመልከቱ እና ባዶ ቦታዎቹን በተገቢው መልስ ሙሉ።

- ማርቆስ 3፥13-19 ማነው የወንጌል አደራ የሰጠው? ወንጌሉን የተቀበለው ማነው?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

- ማርቆስ 5፡1-20 (አስቀድሞ በአጋንንት ተይዞ የነበረው ሰው ላይ አተኩሩ፤ ከቁጥር 18-20)ማነው የወንጌል አደራ የሰጠው ማነው? አደራውን የተቀበለውስ ማነው?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

- ዮሐንስ 1፥40-42፤ ማነው የወንጌል አደራ የሰጠው? ወንጌሉን የተቀበለውስ ማነው?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

- ዮሐንስ 4፡7-42 (ለክርስቶስ ቃል ሴትዮዋ የሰጠችው መልስ ላይ አተኩሩ ቁ. 28-30 እና 39-43)

  ማነው የወንጌል አደራ የሰጠው? ወንጌሉን የተቀበለውስ ማነው?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

- 2ኛ ጢሞቴዎስ 2፥2፤ ማነው የወንጌል አደራ ሰጪው? ወንጌሉን የተቀበለውስ ማነው?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**የጸሎት ጥቆማ፤** “ጌታ ኢየሱስ ላውቅህ እፈልጋለሁ። በዙሪያዬ ያሉትን የግንኙነት መረቦች ማየት እንድችል እርዳኝ፤ ደግሞም ወንጌሉ ወደ ፊት መሄድ እንዲችል በእኔ ኑር። በኢየሱስ ስም ጸለይኩ፤ አሜን!”

**ለተጨማሪ ጥናት የሚሆኑ ምንባባት፤** ሉቃስ 5፥27-32፣ የሐዋርያት ሥራ 10፣ የሐዋርያት ሥራ 16፥22-33።

ማስታወሻ፤

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

## 4ኛ ቀን፥ የወንጌሉን አደራ ማስተላለፊያ ቀላሉ መንገድ

*እኔም፥ ወንድሞች ሆይ፥ ወደ እናንተ በመጣሁ ጊዜ በቃልና በጥበብ ብልጫ ለእግዚአብሔር ምስክርነቱን ለእናንተ እየነገርሁ አልመጣሁም። በመካከላችሁ ሳለሁ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር እርሱም እንደተሰቀለ ሌላ ነገር እንዳላውቅ ቆርጬ ነበርና። እኔም በድካምና በፍርሃት በብዙ መንቀጥቀጥም በእናንተ ዘንድ ነበርሁ፤ እምነታችሁም በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን፥ ቃሌም ስብከቴም መንፈስንና ኃይልን በመግለጥ ነበረ እንጂ፥ በሚያባብል በጥበብ ቃል አልነበረም።* 1ኛ ቆሮንቶስ 2፥1-5

አሁን ሦስት ተቀዳሚ ክፍልፋዮች ይዘናል፡

1. **ተልእኮው ወንጌሉን አደራ መስጠት ነው።** ወንጌሉ ለሌሎች በአደራ ሲተላለፍ ደቀ መዛሙት ይፈራሉ፤ ታላቁ ተልእኮም እውን ይሆናል።
2. **መልእክቱ የመንግሥቱ ወንጌል ነው።** የወንጌሉን የማዳን ክፍል ብቻ የምናካፍል ከሆነ ስለ ክርስቶስ ውሳኔዎች እንዲደረጉ ብቻ ነው ያደረግነው እንጂ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት እንዲሆኑ አይደለም። ወንጌሉ ስለ መንግሥቱ የምስራች ዜና ነው።
3. **የመጀመሪያ የተልእኮ መስኮቻችን የግንኙነት መረቦቻችን ናቸው።** ወንጌሉን ለአዲስ ሰዎች ማካፈላችን እንዳለ ሆኖ በአዲስ ኪዳን በተሰጠው የመሄጃ አቅጣጫ የመጀመሪያው በግንኙነት መረቦች ውስጥ መሥራት ነው።

እናንተም እንደኔ ከሆናችሁ ወደ አእምሮአችሁ የሚመጣው የመጀመሪያው ጥያቄ፥ “እንዴት እንጀምራለን?” የሚል ነው። ዓለም ግዙፍ ናት፤ መልእክቱ ሁሉን የሚያቅፍ ነው፣ ብሎም ጊዜው አጭር ነው።ያለንን መረጃ እንዴት በተግባር ልንወስደው/ ልንይዘው እና በጉልህ ልንኖረው እንችላለን?

መልሱ የሐዋርያው ጳውሎስን ምሳሌ እንደመከተል ያለ ያን ያህል ቀላል ነው። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በተናገረ ጊዜ ትምህርቱ “ክርስቶስ እና የተሰቀለው ክርስቶስ” ላይ ነበር ያተኮረው። በተወሰኑ መንገዶች ጳውሎስ በርካታ ነገሮችን ከመንግሥቱ አሳብ ውስጥ አውጥቶ የጣለ ሊመስል ይችላል። ስለ እምነትስ? ስለፍቅርስ? ስለመንፈሳዊ ስጦታዎችስ? ስለተልእኮ እና ስለአገልግሎትስ? ስለጸሎት እና ምስጋናስ? ጳውሎስ አንድ መልእክት ብቻ እስከማካፈል ድረስ እንዴት ያን ያህል ባለ ጠባብ አስተሳሰብ ይሆናል?

ለዚህ ጥያቄ መልሱ በክርስቶስ እና በእርሱ መንግሥት መካከል ባለው ግንኙነት ውስጥ ይገኛል። ክርስቶስን በመከተል እና ክርስቶስን በማወቅ ላይ ስናተኩር እርሱ ወደ እምነት፣ ተስፋ፣ ፍቅር፣ አገልግሎት፣ ጸሎት፣ ምስጋና፣ ወዘተ . . . ይመራናል። ወንጌሉን በአደራ ለማስተላለፍ ለመቻል በሁሉም የክርስትና ሕይወት አቅጣጫዎች የግድ ምሑራን ልንሆን አይጠበቅብንም። እንዲያውም

ካልተጠነቀቅን ከእውቀት አንጻር በጣም ብቁ ሆነን ከመንፈሳዊ ነገር አንጻር ግን ያልበቃን ልንሆን እንችላለን። በዚህ እርግጠኛ ሆናችሁ እረፉ! **የመንግሥቱ ዝርዝር ተግባራት ንጉሡን በመከተል ሂደት የሚታወቁ ናቸው።** ለምን? ምክንያቱም መንግሥቱ የንጉሡን ልብ የሚይዝ ስለሆነ ነው።

ይሄ ለናንተ እና ለኔ ምን ማለት ነው? ይህ ማለት የኛ ሥራ ክርስቶስን መከተል እና የተማርነውን ማካፈል ነው። በእምነት፣ በአመኔታ እና በትዕግስት ክፍለ ጊዜ ውስጥ እየተጓዛችሁ ካለ እርሱ እያስተማራችሁ ያለውን ለሌሎች አስተምሩ። ክርስቶስን ከተከተላችሁ እና ስለ ባለአደራነት ከተማራችሁ እነዚያን ትምህርቶች በዙሪያችሁ ላሉ ለሌሎች በአደራ አስተላልፉ። እግዚአብሔር የተለያዩ የጸሎት መርሆዎችን እያስተማራችሁ ከሆነ እነዚያን መርሆዎች ከጓደኞቻችሁ ጋር፣ ከቤተሰብ አባላት ጋር፣ ወይም በእናንተ የግንኙነት መረብ ውስጥ ላሉ ለሌሎች አካፍሉ። እግዚአብሔር የወንጌል አደራውን ከመቀበላችን በፊት የክርስተና ዲግሪ እንድንይዝ እየጠየቀን አይደለም። እርሱ የሚፈልገን እንድንከተለው ነው፤ እናም አብረን እየተጓዝን እያለ የተማርነውን ለሌሎች ማካፈል አለብን።

- 1ኛ ቆሮንቶስ 2፥1-5ን እንብቡ እና የጳውሎስን የአስተሳሰብ ሁኔታ የሚያሳዩ ሦስት ወይም አራት ቃላት ጻፉ። ጳውሎስ እንደ አንድ መካከለኛ ሰው ነው? ወይስ እንደ ፍርሃት አልባ መሪ ነው የሚናገረው? ጳውሎስ ያደረገውን ማድረግ ትችላላችሁን?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**የጸሎት ጥቆማ፤** "ጌታ ኢየሱስ ላውቅህ እፈልጋለሁ። አንተን እያወቅሁ ስሄድ የተማርኩትን ከሌሎች ጋር እንድከፋፈል ድፍረትን ስጠኝ። በኢየሱስ ስም ጸለይኩ፤ አሜን!"

**ለተጨማሪ ጥናት የሚሆኑ ምንባባት፤** 1ኛ ቆሮንቶስ 1፥17-31፣ ዮሐንስ 17፥3፣ ዮሐንስ 15፥1-8።

ማስታወሻ፤

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

## 5ኛ ቀን፥ የወንጌሉ የላቀ መስፋት ወይም ታላቅ እድገት

*“ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ይህ የደረሰብኝ በእውነት ወንጌልን ለማስፋት እንደ ሆነ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ።”* ፊልጵስዩስ ፤፥12

ልጅ እያለሁ ሚሲናውያን የሚናገሩባቸው እሁዶችን እጠላ ነበር። ዘግናኝ እንደሚሆን አውቃለሁ ነገር ግን ታማኝ ሆኜ ለመናገር መሞከሬ ነው። እንዲህ የሆንኩት ሚሲዮናውያኑን ስለምጠላ ወይም እነርሱ የሚወክሉትን አገልግሎትን ስለምጠላ አይደለም፤ ያ የሆነው ሁልጊዜ እግዚአብሔር ተመሳሳይ ነገር እንዳደርግ እንደሚጠራኝ ስለሚሰማኝ ነው።

ሚሲዮናዊው በአፍሪካ፣ በህንድ፣ በደቡብ አሜሪካ ወይም በአንታርክቲካ ያገልግል ምንም ለውጥ የለውም። እነርሱ ሁልጊዜ የሚናገሩት ስለ ወንጌሉ ሲሉ በጽናት ስላለፏቸው ነገሮች ነው። አንዱ ሰው በሩዝ እና በውሃ ብቻ ለወራት ስለመኖር ያወራል። ሌላ ሰው ከባድ በሽታን እንዴት እንደታገሉ እና የጠንቋይ ኃይላትን እንዴት እንደተዋጉ ይናገራል። ሌላ ሚሲዮናዊ ደግሞ ለዓመታት ተመሳሳይ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ሲገለግሉ እንደኖሩ እና ለዚህ ሁሉ ልፋታቸው ያዩት በጣም ጥቂት ፍሬ እንደሆነ ይናገራል። በኔ አእምሮ ታሪኮቹ ሁሉ አንድ መመሳሰል አላቸው፤ መከራን መቀበል!

እኔ መከራ ለመቀበል ጽኑ አይደለሁም። በእርግጥ በተቻለኝ አቅም ሁሉ ላስወግደው እሞክራለሁ። ነገር ግን የወንጌሉ እድገት ሂደት በአዳጋች ሁኔታዎች የሚታጨቅባቸው ጊዜያት አሉ። ወንጌሉን ለሌሎች አደራ ስለመስጠት የጸና አቋም ካለን አንድ ጥያቄ ልንመልስ ይገባናል። “ለወንጌሉ መስፋፋት ስል ለመጽናት ምን ያህል ፈቃደኛ ነኝ?”

ለዚህ ጥያቄ መልሱ እንደየሰዉ የተለያየ ነው። ኢየሱስ በመስቀል መከራ ጸና፤ (ዕብ. 12፥1-3)። ጳውሎስ እስራትን፣ ድብደባን፣ እና በጊዜ ሂደት መሞትን ተቋቋመ፤ (2ቆሮ. 11፥23-28)። እነዚህ ሁለት በጣም ጽንፈኛ ምሳሌዎች ናቸው። በአሜሪካ አብዛኛዎቹ ክርስቲያኖች እንደዚህ ዓይነት መከራዎችን ፈጽሞ እንደማያገኟቸው ዕድሉ ሰፊ ነው። ነገር ግን የቤተሰብ መለያየት፣ የገንዘብ ጉድለት፣ የድብርት ስሜት፣ የተለያዩ መጠን ያላቸው ችግሮች፣ የጠላት ጥቃት እና ምንም ያህል የበዙ አነስ ያሉ የማይመቹ ሁኔታዎችን መቋቋም ያልተለመደ አይደለም።

አሳቤ ቀላል ነው! የወንጌሉ መስፋፋት ከሰይጣን ተቃውሞ ጋር ይጋፈጣል። በጳውሎስ ሁኔታ የእርሱ ገጠመኞች (እስራት፣ መከራ፣ ድብደባ፣ ወዘተ፥) ‘*በእውነት ወንጌልን ለማስፋት*’ ውለዋል። ጳውሎስ እነዚያን መከራዎች ባይቋቋም ኖሮ ወንጌሉ የሄደበት ርቀት ድረስ ባልሄደም ነበር።

ምንም እንኳን መከራን በዚያ ልክ ተቀብለን ለመቋቋም ፈጽሞ ባንጠራም እንኳ፥ ትናንሾቹ የሕይወት መከራዎቻችን ለወንጌሉ መስፋፋት ዕድል ይፈጥራሉ። እራሳችንን ከችግሮች አንጻር የምንገራበት መጠን አብዛኛውን ጊዜ ወንጌሉ የሚስፋፋበትን መዳረሻ ስፋት መጠን ይወስናል።

አስታውሱ፤ በምትጋፈጧቸው ሁኔታዎች ሁሉ ውስጥ ዓለም እያያችሁ ነው። ለእርሱ ክብርን ለመቀበል እንዲያመች እግዚአብሔር በወሳኝ ስፍራ ነው ያስቀመጣችሁ።

- የሕይወትን ግፊቶች እና መከራዎች የምትይዙበትን አያያዝ ሰዎች ሲያዩ የእግዚአብሔርን ተጽእኖ ይረዳል ወይስ ይጎዳል? የእናንተ ምላሽ እንዴት አድርጎ ክርስቶስን ያከብራል ብሎም ሌሎችን ወደ እርሱ ይመራል?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

- በአስቸጋሪ ጊዜያት አልፎ ሆኖም ጠንካራ ድፍረትን እና በክርስቶስ ያለውን እምነትን የጠበቀ በሕይወታችሁ ያለ አንድ ሰው ጥቀሱ። የእርሱ ወይም የእርሷ ምሳሌነት እንዴት በሕይወታችሁ ላይ ተጽእኖ አሳደረ?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**የጸሎት ጥቆማ፤** “ጌታ ኢየሱስ ላውቅህ እሻለሁ። ለወንጌሉ ወደ ፊት መሄድ ዓላማ በሕይወቴ መከራዎች እና ችግሮች በኔ አቅጣጫ እንዲመጡ እንደምትፈቅድ ተረድቻለሁ። በኔ ምሳሌነት ተነክተው ወደ አንተ እስኪሳቡ ድረስ ይህን ዓይነት የጸና ሕይወት እንድኖር እርዳኝ። በኢየሱስ ስም ጸለይኩ፤ አሜን!”

**ለተጨማሪ ጥናት የሚሆኑ ምንባባት፤** የሐዋርያት *ሥራ* 8፥1-4፣ የሐዋርያት *ሥራ* 4፥1-31፣ ሉቃስ 21፥12-19።

ማስታወሻ፤

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

## 6ኛ ቀን፥ በ 'ከ . . . እስከ . . .' መስመር ምን ታደርጋላችሁ?

*"በወንጌልም ማኅበረተኛ እሆን ዘንድ ስለ ወንጌል ሁሉን አደርጋለሁ።"* 1ኛ ቆሮንቶስ 9፥23

አንድ አባት ለልጁ እንዲህ ሲል አብራራ "በእያንዳንዱ መቃብር ስፍራ ውስጥ ምስጢር አለ።" በዐረፍተ ነገሩ ግራ አጋቢነት የተነሣ ልጁ ተጠግቶ አደመጠው። "በመቃብር ስፍራ ውስጥ ያለው ምስጢር በእያንዳንዱ የመቃብር ድንጋይ ላይ ያለው በልደት እና ሞት መካከል ያለው መስመር ነው።" ሁለቱ አብረው ተጨማሪ ጥቂት እርምጃዎችን ሄዱ እና "በውልደት ቀን እና በሞት ቀን መካከል (ከ. . . እስከ. . .) የሚገልጥ አጭር መስመር አለ። ሕይወት በአስፈላጊነት ለእያንዳንዱ ሰው ተመሳሳይ ነው። ተወለድን፣ ኖርን እና እንሞታለን። በኖረ ሰው እና ከበስተኋላው የሚዘከርለት ነገር በተወ ሰው መካከል ያለው ልዩነት በዚያ 'ከ. . . እስከ. . .' ምን ማድረጋቸው ነው።"

በ'ከ. . . እስከ. . .' ምን ታደርጋላችሁ? ጳውሎስ "ስለ ወንጌል ሁሉን አደርጋለሁ" አለ። ጳውሎስ ወደ ኋላ ዞሮ የራሱን ሕይወት ሲመለከት ከፍታዎች እና ዝቅታዎች ነበሩት፤ መከራዎች እና ድሎች ነበሩት፣ ሕመሞች እና ዕድገቶች ነበሩት። ነገር ግን በጳውሎስ ትዝታ የማይገኝ አንድ ነገር አለ፤ ቁጭት! "መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፤" (2ኛ ጢሞቴዎስ 4፥7)።

የጳውሎስ ሕይወት ያለ ቁጭት የሆነው "ሁሉን ስለ ወንጌል" ከማድረግ ጋር በተያያዘ እንደሆነ ምንም ጥያቄ የለውም። ጳውሎስ የራሱን 'ከ. . . እስከ. . .' በሙሉ አቅሙ ተጠቅሞበታል። በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "እግዚአብሔር በዚህ ምድር እንዳደርግ ያስቀመጠኝን ነገር በሙሉ አድርጌያለሁ።" ያሉ ሁለት ሰዎች ብቻ አሉ። የመጀመሪያው ኢየሱስ ነበር፤ ሁለተኛው ጳውሎስ ነው። (ዮሐንስ 19፥30፤ ዕብራውያን 10፥11-12፤ 2ኛ ጢሞቴዎስ 4፥7) የእናንተ ታሪክ እንዴት ያልቅ ይሆን?

ክርስቶስ ተከታዮቹ አሕዛብን ደቀ መዛሙርት እንዲያደርጉ መሾሙን እናውቃለን፤ (ማቴ. 28፥19)። በአጠቃላይ ምልከታ ሁላችንም ተመሳሳይ ዓላማ አለን። በሕይወት ያለንበት ስፍራ ሳይገድበን ወንጌሉን ለሌሎች በአደራ ማስተላለፍ አለብን። ክርስቶስ ሕይወቱን የሰጠው እኛ ወንጌሉን እንድናገኝ ነው። ጳውሎስ ሕይወቱን ያዋለው ለወንጌሉ ነው። እኔና እናንተስ እግዚአብሔር በሰጠን ሕይወት ምን እናደርጋለን?

አባት ሆይ ዓላማ ስጠኝ፥ የሆነ ጥልቅ፥
በደስታም ይሁን በኀዘን ቃልህን እንድጠብቅ፤
ትግሉን የሚያሸንፍ፥ ታማኝ እና የእውነት፥
በየዕለቱ ሕይወቴ አንተን የሚያስደስት፤
አንድ ሕይወት ብቻ አለኝ ያም በቅርቡ ያልፋል
ለክርስቶስ የሠራሁት ብቻ ለዘላለም ያርፋል።

እንደ ክርስቶስ ተከታዮች በዓለም ላይ ላለው ታላቅ ፍለጋ ሕይወታችንን የመስጠት ዕድል አግኝተናል። እግዚአብሔርን ልናውቀው እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያውቁት ልናደርግ እንችላለን። እግዚአብሔርን ለማወቅ እና ደቀ መዛሙርት ለማፍራት ያለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሂደት በጣም ቀላል ነው። እግዚአብሔርን ውደዱ! ዓለምን አገልግሉ! ወንጌሉን ለሌሎች አደራ ስጡ!

- በአንድ ዐረፍተ ነገር ከበስተ ኋላ ትታችሁ ልትሄዱ የምትፈልጉትን የሚዘከርላችሁን ነገር ግለጹ፤

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

- ወንጌሉን ለሌሎች በአደራ ማስተላለፍን እንዴት የሕይወታችሁ የላቀ ታላቅ አካል ማድረግ ትችላላችሁ?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**የጸሎት ጥቆማ፤** "ጌታ ኢየሱስ ላውቅህ እፈልጋለሁ። በዚህ ምድር እንዳደርግ ያስቀመጥኸኝን ነገር ሁሉ አሳክቼ መኖር እንድችል በእኔ ውስጥ እንድትኖር እጸልያለሁ። የኋላ ታሪኬ አንተን በማወቅ እና ሌሎችን ከአንተጋር ወዳለ ግንኙነት እንዲገቡ እና ባላቸው ግንኙነት እንዲያድጉ በማድረግ የሚጠቀስ እንዲሆን እፈልጋለሁ። በኢየሱስ ስም ጸለይኩ፤ አሜን!"

**ለተጨማሪ ጥናት የሚሆኑ ምንባባት፤** ማርቆስ ፩፥32-39፣ ፩ኛ ቆሮንቶስ ፱፥13-27።

ማስታወሻ፤

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

# የክርስቶስ ሕይወት መርጃዎች / መገልገያዎች

ስለ የግንኙነት ሕይወት እና የክርስቶስ ሕይወት አስደናቂ ነገሮችን ለማየት ዓይኖቻችሁ ከተከፈቱ በኋላ ወደ ሞተ ሃይማኖት መመለስ የለም። አሁን ጥያቄው "የበለጠ ለመማር ወደ የት መሄድ ይኖርብኛል?" የሚል ይሆናል።

ጠንካራ የኅብረት አትኩሮት ያላቸውን መጻሕፍት ዝርዝርም እዚህ አካትተናል። ከእነዚህ መጻሕፍት እንዳንዶቹ ከኅትመት ውጪ ሆነዋል ነገር ግን በአሮጌ ተራ የመጻሕፍት መደብሮች ሊገኙ ይችላሉ። ከእነዚህ ደራሲያን የተወሰዱት ቁልፍ አሳቦች ወንጌሉ ይህ ነው በሚለው በዚህ ትምህርት ውስጥ ቀርበዋል።

አንዳንዶቹ መጻሕፍት የዚህ የጥሞና መምሪያ አዘጋጆች ያልተቀበሏቸውን ትምህርቶች ያቀርባሉ። ለምሳሌ፥ ስታንፎርድ አማኞች ኃጢአተኛ ተፈጥሮንም ሆነ አዲሱን ፍጥረት ሁለቱም (በአንድ ጊዜ) ይኖሯቸዋል ብሎ ያስተምራል። እኛ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት በዚህ አንስማማም። ማክቬይ፣ ፎስተር እና ጆርጅ በየራሳቸው መጽሐፍ ጠንካራ ተቃውሞን ያቀርባሉ። እኛ እንዚህን መጻሕፍት በዝርዝሩ ውስጥ ያካተትናቸው በሌሎች የኅብረት ጉዳዮች ላይ የተረጋገጡ ምልከታዎችን ስለሚያቀርቡ ነው። ስታንፎድ እግዚአብሔር አማኝን ወደ እውነት የሚያደርስበት ሂደት ዙሪያ ከሚጽፉት ጸሐፍት መካከል ከታላላቆቹ አንዱ ነው። ጥቂት ልዩነቶች መኖራቸው እንዳለ ሆኖ የበሰለ አማኝ በቅዱስ ቃሉ ብርሃን ስሕተትን ለመለየት ችግር አይኖርበትም።

እነዚህን መጻሕፍት ስታነቡ፤ በኅብረት ላይ ቁልፍ የሆኑ ጽንሰ አሳቦችን ለማግኘት ሞክሩ። ክርስቶስ በእናንተ ሕይወት ውስጥ፥ በእርሱ መኖር፥ ሕይወት ከማድረግ ይልቅ መሆን፥ እግዚአብሔርን ማወቅ፥ ከክርስቶስ ጋር መቆራኘት፥ የእግዚአብሔር በእናንተ ውስጥ መኖር፥ ዐውዳዊ እውነት ወይም በክርስቶስ የሆነ እውነት የሚሉ ሃረጎችን አትኩሮት ሰጥታችሁ ማስታወሻ ያዙ። እነዚህ ሐረጎች ወደ ተትረፈረፈ ኅብረት ይመሯችኋል።

## የተጠቆሙ መገልገያዎች ዝርዝር

- *Grace Walk* by Steve McVey
- *The Complete Green Letters* by Miles Stanford
- *Because We Love Him* by Clyde Cranford
- *Transformed Into His Image* by David Foster
- *Grace Amazing* by Steve McVey
- *Complete in Christ* by Bob George
- *The Explicit Gospel* by Matt Chandler
- *The Rest of the Gospel* by Stone and Gregory
- *Laws for Liberated Living* by Manley Beasley
- *Classic Christianity* by Bob George
- *Calvary Road* by Roy Hession
- *The Indwelling Life of Christ* by W. Ian Thomas
- *Truefaced* by Thrall, McNicol Lynch
- *Renovation of the Heart* by Dallas Willard
- *Alive By His Life* by Manley Beasley
- *The Law of Liberty in the Spiritual Life* by Evan Hopkins
- *Born Crucified* by L.E. Maxwell
- *Grace Rules* by Steve McVey
- *Falling for God* by Gary Moon
- *Not I But Christ* by Stephen Olford
- *Gospel* by J. D. Greear
- *Jesus + Nothing = Everything* by Tullian Tchividjian
- *Jesus Changes Everything* by Bob George
- *To Live is Christ To Die is Gain* by Matt Chandler

## ጥያቄዎች ካሏችሁ በዚህ አድራሻ እባካችሁን አግኙን፤

info@lifebaptistchurch.com


thisistheGospel.com